
# አካባቢ ሳይንስ

# ማስተማሪያ መጽሐፍ



# ሦስተኛ ክፍል

**2004** ዓ/ም

## ማውጫ


| ተ.ቁ | | ገጽ |
|---|---|---|
| | መግቢያ | i |
| **1** | ክፍለ ትምህርት አንድ፡- ምግብና የቤተሰብ ደህንነት | **1** |
| | 1.1. ምግብ | **2** |
| | **1.2.** የቤተሰብ ጽዳት | **11** |
| | **1.3.** የእረፍት ጊዜና መዝናናት | **18** |
| **2** | ክፍለ ትምህርት ሁለት፡- ተፈጥሮአዊ አካባቢያችን | **25** |
| | **2.1.** የተፈጥሮ ሀብት | **2 6** |
| | **2.2.** ኃይል | **34** |
| | **2.3.** ጉልበት | **37** |
| **3** | ክፍለ ትምህርት ሦስት ፡- በማህበረሰባችን ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት | **43** |
| | **3.1** እርሻ | **44** |
| | **3.2.** የአካባቢ ኢንዱስትሪ ምርቶች | **60** |
| **4** | ክፍለ ትምህርት አራት፡- ክልላችን | **65** |
| | **4.1.** የክልላችን መገኛ | **66** |
| | **4.2.** ዋና ዋና የመሬት አቀማመጥ | **69** |
| | **4.3.** ክልላዊና ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማዎች | **73** |
| | **4.4.** አስተዳደራዊ መዋቅሮች | **75** |
| | **4.5.** ቅርሶች | **78** |
| | **4.6.** በክልሉ አገር ወዳድነት | **82** |

## መግቢያ

ይህ የሦስተኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ የማስተማሪያ መጽሐፍ ለደረጃው በተዘጋጀው የመማሪያ መጽሐፍ የተካተቱትን የትምህርት ይዘቶች መምህራን ለተማሪዎቹ በሚገባቸው ዘዴ ለማስተማር እንዲችሉ በአጋዥነት እንዲጠቀሙ የተዘጋጀ ነው።

መጽሐፉ አራት ዋና ዋና ክፍለ ትምህርቶችን የያዘ ነው። እነዚህም ምግብና የቤተሰብ ደህንነት፣የአካባቢያችን ተፈጥሮ፣ በማህበረሰባችን ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትና የክልላችን መገኛ የሚሉ ሲሆኑ በእያንዳንዱ ክፍለ ትምህርትም ሥር ዘርዘር ብለው የቀረቡ ጠቃሚ ጉዳዮች ተካትተዋል።

የትምህርቱ ዋና ዓላማ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ያገኙትን እውቀት በአካባቢያቸው ከሚያገኙት እውቀት ጋር አዋህደው ማህበራዊና ተፈጥሯዊ ጉዳዮችን በተሟላ ሁኔታ እንዲገነዘቡ ለማድረግ ነው። በመሆኑም መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አሳታፊ ዘዴን በመጠቀም ከቀረቡት የማስተማር ዘዴዎች በተጨማሪ ሌሎችንም ምቹ ዘዴዎች በመምረጥ መሠረታዊ እውቀት ማስጨበጥና ለቀጣዩ ደረጃ ጠንካራ መሠረት የሚያዘጋጅ ሆኖ እንዲቀርብና የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

# ክፍለ ትምህርት አንድ

# ምግብና የቤተሰብ ደህንነት

የተመደበው ጊዜ **45** ክፍለ ጊዜ

*መግቢያ*

በዚህ ክፍለ ትምህርት ስለምግብ፣ስለቤተሰብ ጽዳትና ስለእረፍት ጊዜና መዝናናት የሚያብራሩ የትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል። እነዚህ የትምህርት ይዘቶች በአቀራረባቸው የተለያዩ ቢመስሉም ለቤተሰብ ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር ሲታዩ ተደጋጋፊዎች ናቸው። ለቤተሰብ ደህንነት ምግብ፣ የግልና የቤተሰብ ጽዳት እንዲሁም የእረፍትና የመዝናኛ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ውስጥ አስፈላጊነታቸው ከፍተኛ ነው።

ምግቦች በአራት ክፍሎች መከፈላቸውን፣ከነዚህም ክፍሎች የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት እንደሚቻል፣የምግብ መበከል ለጤና ጠንቅ መሆኑን፣ የግል፣የቤተሰብና የአካባቢ ጽዳት አጠባበቅ፣የምግብና የውሃ ንፅህና ጉድለት የሚያስከትሏቸው በሽታዎችና መከላከያቸው እንዲሁም የኤድስ በሽታ በተማሪዎች፣በቤተሰብና በህብረተሰቡ ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ የሚሉት ጉዳዮች በዝርዝር ቀርበዋል።

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት ለቤተሰብ ህይወት ጠቃሚ የሆኑ ጉዳዮች በመማር ማስተማር ሂደት አሳታፊ ዘዴዎችን በመጠቀም የታለመላቸውን ግብ ለመምታት እንዲቻል የመምህሩን /ሯን/ ብርቱ ጥረት ይጠይቃል።

**አጠቃላይ ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- አራቱን መሠረታዊ የምግብ ክፍሎችንና የተመጣጠነ ምግብ አመጋገብ ሥርዓትን ይገልፃሉ።
- የምግብ ብልሽት ምክንያቶችንና ውጤታቸውን ይዘረዝራሉ።
- የቤተሰብ ጤና አጠባበቅና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅን ይለማመዳሉ።
- ጥሩ ባልሆነ የቤተሰብ ጤና አጠባበቅ ምክንያት የሚፈጠሩ በሽታዎችን ይዘረዝራሉ።
- የኤች አይ ቪ ኤድስ ህመም በቤተሰብና በህብረተሰብ ላይ የሚያስከትለውን ችግር ይገልፃሉ።
- ከኤድስ ጋር አብረው ለሚኖሩ ሰዎች ፍቅርና እንክብካቤ ያሳያሉ።

- በትርፍ ጊዜ ከቤተሰብ ጋር መዝናናት አስፈላጊ እንደሆነ ይገልፃሉ። ትርፍ ጊዜአቸውን በአግባቡ ይጠቀማሉ።
- ሳይንሳዊ ክህሎትን ያሳያሉ። አካባቢን በመመልከት በመመዝገብ፣ በመመደብ፣በመጠየቅ፣በመለካት፣ሙከራንና ማጠቃለያ በማቅረብ ግንኙነትና አብሮ የመሥራት ክህሎትን ያዳብራሉ።

## 1.1. ምግብ

የተመደበው ጊዜ **20** ክፍለ ጊዜ

**1.** ዝርዝር ዓላማዎች፡**-** ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- አራቱን ዋና ዋና የምግብ ክፍሎችን ይዘረዝራሉ
- የአራቱን የምግብ ክፍሎች ጠቀሜታ ይገልፃሉ
- የተመጣጠነ ምግብ ማለት የምንመገበው ምግብ አራቱን ክፍሎች መያዙ እንደሆነ ያስረዳሉ።
- የተመጣጠነ ምግብን አመጣጥነው መመገብ ይለማመዳሉ።
- የምግብ ብልሽት ምክንያቶችን ለይተው ይገልፃሉ።
- የምግብ ብልሽት ውጤቶችን ይዘረዝራሉ።
- የምግብ መበከልን ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎችን ይለያሉ።

**2.** ዝርዝር ይዘቶች

- የአመጋገብ ሥርዓት፣
- አራቱ ዋና ዋና የምግብ ክፍሎች፣
- የምግብ መበከል ምክንያቶች፣
- የምግብ ብክለትን መከላከል።

መግለጫ

ምግብ ማለት ማንኛውም ለሰውነታችን ጠቃሚ ንጥረ ነገሮችን የያዘና በፈሳሽ ወይም በጠጣር መልክ የሚወሰድ ነገር ሁሉ ማለት ነው። ምግብ ለሰውነት የሚከተሉትን ጥቅሞች ይሰጣል።

- ለአካል ዕድገት፣

- ለጤንነት፣

- ለሰውነት ግንባታና ለአእምሮ ንቃት፣

- ኃይልና ሙቀት ለመስጠት።

የምግብ አመጋገብ ሥርዓትና የምግብ ዓይነቶች ማለትም የባህላዊ ምግቦችም ሆኑ የዘወትር ምግቦች ከቦታ ቦታ ይለያያሉ።

ሰውነታችን ጤናማና ጠንካራ ሆኖ የእለት ተዕለት ተግባራችንን በብቃት ለማከናወን የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ያስፈልገዋል። የተመጣጠነ ምግብ ማለት መጠኑ በቂ የሆነና የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን የያዘ ምግብ ማለት ነው።

የተመጣጠነ ምግብ ለማግኘት በየዕለቱ ገንቢና ጠጋኝ፣ጉልበትና ሙቀት ሰጪ እና በሽታ ተከላካይ ምግቦችን መመገብ አለብን። የምግብ ዓይነቶች በአራት ዋና ዋና የምግብ ክፍሎች ይከፋፈላሉ።

እነዚህም፡- የእህልና ጥራጥሬ፣

- የአትክልትና ፍራፍሬ፣

- የሥጋና

- የወተት ክፍሎች በመባል ይታወቃሉ።

የምንመገበው ምግብ በንፅህናና በጥንቃቄ ካልተጠበቀ ሊበከል ይችላል። ለምግብ ብክለት መንስኤዎችም ጥቃቅን ተህዋስያን /ጀርሞች/ ዝንቦች፣በረሮዎች ወዘተ ናቸው። እንደ ባክቴሪያ ያሉ ጥቃቅን ጀርሞች ምግብ ውስጥ ሲገቡ ምግቡን ይመርዛሉ። መጥፎ ጠረን እንዲኖረውና ጣዕሙም እንዲቀየር ያደርጋሉ።

የምግብ ብክለት ሲከሰትም ለተለያዩ በሽታዎች ይዳርጋል።

ለምሳሌ፡- ለኮሌራ፣ለአሜባ፣ለጃርዲያ፣ለተቅማጥና ትውከት በሽታዎች።

ምግብ ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ ማቆየት የሚያስችሉ ዘዴዎች አሉ። እነዚህም፡-

ሥጋን በማድረቅ

- ጨው በመነስነስ

- በማቀዝቀዛ ውስጥ በማቆየት፣

ወተትን - በማፍላት /ፓስቸራይዜሽን/

- በማቀዝቀዣ ውስጥ በማስቀመጥ፣

የበሰሉ ምግቦችን - በንፁህ ዕቃ ውስጥ በማድረግ ከድኖ በማስቀመጥ፣

- በአየር ውስጥ የሚገኙ በሽታ አምጪ ተህዋስያንና ትናንሽ ነፍሳት እንዳይገቡ መከላከል ናቸው።

## 3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

- በቅድሚያ ዋናውን ርዕስ ያስተዋውቁና ተማሪዎች በትምህርቱ ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት የሚያገኟቸውን ቁልፍ ቃላት እያነበቡላቸው ያስተዋውቋቸው።
- ምግብ ወደሚለው የመጀመሪያ ርዕስ ይግቡና ለማነቃቂያነት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎቹ እንዲነጋገሩና ለመመለስ እንዲሞክሩ ጊዜ ይስጧቸው።
- የምግብ አስፈላጊነትን ከዚህ በፊት ከተማሩት ትምህርት የሚያስታውሱትንና በአካባቢያቸው ዘወትር የሚመገቧቸውን የምግብ ዓይነቶች አስበው እንዲናገሩ ያደፋፍሯቸው። ተማሪዎቹ የሚሰጡትን ሃሣብ አድንቀው ከተቀበሉ በኋላ ጤናማና ደስተኛ ሆኖ ለመኖር ምግብ እንደሚያስፈልግ፣ ማንኛውም የሚበላና የሚጠጣ ነገር ለሰውነት ጠቃሚ ንጥረ ነገሮችን የሚያበረክት ሁሉ ምግብ እንደሚባል ያስረዷቸው። በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በምሳሌነት የተዘረዘሩትን የምግብ ዓይነቶች የሚያካትት መሆኑን ይግለጹላቸው።
- በአካባቢያቸው ዘወትር የሚመገቧቸው የተለያዩ ምግቦችን እንዲጠሩ መጠየቅና የሚጠሯቸውን የምግብ ዓይነቶች ከተዘረዘሩት ጋር እንዲያነፃፅሩ ያድርጓቸው።
- የምግብ ጥቅሞችን እንዲዘረዝሩ ይጠይቋቸውና ሙከራቸውን ይቀበሏቸው።
- ምግብ በጠጣርነትና በፈሳሽነት መልክ በትኩስነትና ከቀዘቀዘ በኋላ እንደሚወሰድ የተዘረዘሩትን ምሳሌዎች በመጥቀስ ያስረዷቸው።
- በተለያዩ አካባቢዎች /በገጠር ወይም በከተማ/ የተለያዩ የአመጋገብ ሥርዓቶች እንዳሉ ይግለጹላቸው።
- የምንመገባቸው ምግቦች በአራት ዋና ዋና የምግብ ክፍሎች እንደሚከፈሉ እነሱም፡- የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የእህልና ጥራጥሬ፣የሥጋ እና የወተት ክፍሎች ተብለው እንደሚጠሩ ያስረዷቸው። ለእያንዳንዱ ምግብ ክፍልም ምሳሌ እንዲሰጡ ተማሪዎቹን ተራ በተራ ይጠይቋቸውና በመጽሐፉ ከተሰጡት ምሣሌዎች ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው።

- የተለያዩ እንስሳት ሥጋ ለምግብነት ተዘጋጅተው የሚቀርቡትን የምግብ ዓይነቶች ወጥ፣ ክትፎ ፣ጥብስ፣ዱለት .... በማለት በተሰጠው ሠንጠረዥ መሠረት በወረቀት ሞልተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ። እዚህ ላይ በትክክል ሊሞሉም ላይሞሉም ይችላሉ። በመጨረሻም ሠንጠረዡን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመሥራት በሚከተለው መሠረት የምግብ ዓይነቶቹን በመሙላት ያስረዷቸው።

**ሠንጠረዥ 1.1** በልዩ ልዩ መልክ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የእንስሳት ሥጋ

| የሥጋው ዓይነት | ተዘጋጅቶ የሚቀርብበት ምግብ ዓይነት |
|---|---|
| የበሬ ሥጋ | ወጥ፣ጥብስ ክትፎ |
| የበግ/የፍየል ሥጋ | ወጥ፣ ጥብስ ዱለት |
| የዶሮ ሥጋ | ወጥ፣አሮስቶ፣ሾርባ |
| የአሣ ሥጋ | ጥብስ፣ወጥ፣አሣ ለብለብ |

- እያንዳንዱ የምግብ ክፍል ለሰውነት የሚያበረክተውን ጥቅም በመማሪያው መጽሐፍ በተገለጸው መሠረት ያስረዷቸው።
- የተወሰኑ ምግቦችን ብቻ መመገብ ለሰውነት የምግብ ፍላጐት እንደማያሟላና አንድ ሰው ሙሉ ጤናማ ሆኖ ለመኖር ደግሞ በየዕለቱ የሚመገበው ምግብ አራቱን የምግብ ክፍሎችን ያካተተ መሆን እንዳለበት ያስረዷቸው።
- አራቱን የምግብ ክፍሎች እንደ አስፈላጊነታቸውና መጠናቸውን ያካተተ ምግብ ደግሞ የተመጣጠነ ምግብ እንደሚባል እንዲረዱ ያስችሏቸው።
- የተመጣጠነ ምግብ ለምን እንደሚጠቅም ይጠይቋቸውና የሚሰጡትን መልስ ይቀበሉ። ከዚያም
    - ሰውነትን ለመገንባትና ለመጠገን፣
    - ከበሽታ ለመከላከል፣
    - ብርታትና ጥንካሬን ለማግኘት፣

- የዐይን፣የቆዳንና የድድን ጤንነት ለመጠበቅና ሌሎችም ጥቅሞች እንዳሉት ያስረዷቸው። የተመጣጠነ ምግብ ምንጮች በሥዕሉ ላይ ያሉትን አራቱንም ክፍሎች በማየት ለይተው እንዲያውቁ ይርዷቸው።

- ተማሪዎች  የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን እንዲዘረዝሩና ከዘረዘሯቸው የምግብ ዓይነቶች ውስጥ በማቀላቀል የተመጣጠነ ምግብ እንዲያዘጋጁ ያድርጓቸው።
- ተማሪዎች የራሳቸው የሆነ ምግብ ቤት ወይም ሆቴል እንዳላቸው አድርገው የምግብ ዝርዝር በመፃፍ የተመጣጠነ የምግብ ዝርዝር በማቅረቢያው ወረቀት በካርድ እንዲሰሩና አሳምረው እንዲያቀርቡ ያድርጉ።
- የምግብ መበከል ምክንያቶች የሚለውን ርዕስ ሲጀምሩ ስለምግብ መበከል የሚያውቁትን እንዲናገሩ ተማሪዎቹን መጠየቅና የሚመልሱትን ማዳመጥ። ከዚያም በኋላ የምግብ መበከል በዓይን በማይታዩ የተለያዩ ጀርሞች መመረዝ መሆኑን ያስረዷቸው
- በዓይን በማይታዩ እንደ ባክቴሪያ ባሉ ጥቃቅን ጀርሞች የተመረዙ/የተበከሉ/ ምግቦችን መመገብ ደግሞ ለጤና ጠንቅ መሆኑን ያብራሩላቸው።
- አንዳንዴም በትልቅ ግብዣ ወይም ሠርግ ጊዜ የሚያዘጋጀው ምግብ እስከ ሁለት ቀናት ድረስ ሳያልቅ የቆየ ከሆነ በጀርሞች ሊበከል እንደሚችል ማስረዳት።

- የምግብ መበከልን የሚያስከትሉ ምክንያቶች የተለያዩ መሆናቸውን እነሱም፡-
    - የግል ንፅህና ጉድለት፣
    - የውሃ ንፅህና ጉድለት፣
    - የምግብ መሥሪያና መመገቢያ ንፅህና ጉድለት፣
    - በተለያዩ ኬሚካሎች መመረዝና በጥንቃቄ ጉድለት ምግቡ በጥቃቅን ጀርሞች ሲነካካ መሆናቸውን በመዘርዘር ያስረዷቸው።
- የምግብና የውሃ ብልሽት /ብክለት/የሚያመጣውን ችግር በተመለከተ ምግብ በሚዘጋጅበት ጊዜ ንፅህናው የተጠበቀ ካልሆነ ለተለያዩ የምግብና ውሃ ወለድ በሽታዎች ለምሣሌ፡- ለተቅማጥ፣ ለትውከት፣ለኮሌራ፣ለአሜባና ለጃርዲያ እንደሚያጋልጥ ማስረዳት ተገቢ ይሆናል። በሚከሰቱ ተቅማጥና ትውከት ምክንያትም

ሰውነት ውስጥ ያለው ፈሳሽ ሊቀንስ ስለሚችል ፈሳሽ ነገሮችን በመውሰድ መተካት እንደሚገባ እንዲያውቁ ያድርጉ። ህመሞቹ ሲከሰቱም በፍጥነት ህክምና ማድረግ እንደሚገባ ያስገንዝቧቸው።

- የምግብ ብልሽትን መከላከል የሚለውን ርዕስ እያስተዋወቁ ተማሪዎች በቅድሚያ እንዲረዱ የሚፈለገው በተቻለ መጠን ምግብ በንፅህና ጉድለት በጀርሞች እንዳይበከል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ብክለትን ከመከላከል የበለጠ እንደሆነ መግለጽ ነው።
- የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ ከነገሯቸው በኋላ ጥቂቶቹን እንዲናገሩ ያነቃቋቸው

ከዚያም፡- የምግብ ማዘጋጃ ዕቃዎችን ማጽዳት፣

- የእጅና የጥፍሮችን ንፅህና መጠበቅ፣
- ለምግብ ዝግጅት ንፁህ ውሃን መጠቀም፣
- የሚዘጋጀው ምግብ በበቂ ሁኔታ ማብሰል እንደሚያስፈልግ በመዘርዘር መግለጽና እንዲረዱት ማድረግ።

- በተለይ በጥሬነታቸው የሚበሉ እንደ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ ለምግብነት ከመቅረባቸው በፊት በንፁህ ውሃ ማጠብ እንደሚገባና ተማሪዎቹም በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው እነዚህን ምግቦች በሚመገቡበት ወቅት አጥቦ መብላትን እንዲለምዱ ይምከሯቸው።
- በሌላ በኩል ደግሞ ምግብ ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ ማቆየት የሚያስችሉ ዘዴዎች እንዳሉና ተማሪዎችም በቤታቸው ተሞክሮ እንዳለ ይጠይቋቸውና የሚያቀርቡትን ሃሣብ ይቀበሏቸው። በመጨረሻም ምግብ ሳይበላሽ የማቆያ ዘዴዎች፡-
  - ምግብን ማድረቅ፣
  - ምግብን ማቀዝቀዝ፣
  - ወተትን ማፍላት፣
  - ምግብን መቀቀል እንደሆኑ በማብራራት ማስረዳት
- ወተትን በማፍላት በውስጡ ያሉትን ጀርሞች እንዲሞቱና ለረጅም ጊዜ የማቆያ ዘዴ ፓስቸራይዜሽን ተብሎ እንደሚጠራ ያስረዷቸው።

- በመማሪያ መጽሐፉ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ምግብን ለረጅም ጊዜ ሳይበላሽ የማቆያ ዘዴዎችን ተወያይተው እንዲጠቅሱ ያድርጉ

ለምሳሌ፦ ምግብን ጭስ ባለበት ቤት ማድረቅ፡

- ምግብን ማሸግ፣
- ኮምጣጤን መጠቀምና የመሳሰሉት

በመጨረሻም በንዑስ ርዕሱ የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦችን ይከልሱላቸውና ትምህርቱን ያጠናቁ። የቤት ስራ ወይም የቡድን ሥራም ይስጧቸው

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- አራቱን የምግብ ክፍሎች የሚያሳይ ሥዕል፣
- የተለያዩ እንስሳት ሥጋ በተለያየ መልክ የሚቀርቡት የምግብ ዓይነቶች የሚያሳይ ሥዕል፣
- በጥሬነታቸው የሚበሉ ምግቦች የማጠብ ሂደት ሥዕል።

## 5. የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች፦

- ምግብ ለሰውነታችን ለምን ለምን እንደሚያስፈልግ መረዳታቸውን መከታተልና መገምገም፣
- በጠጣርና በፈሳሽ መልክ የምንመገባቸው ምግቦችን ዘርዝረው እንዲናገሩ መጠየቅ፣
- አራቱ የምግብ ክፍሎች ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር እንዲናገሩ መጠየቅ፣
- የተመጣጠነ ምግብ ምንጮችን እንዲዘረዝሩ የክፍል ሥራ መስጠትና መከታተል፣
- የምግብ ብልሽትን /ብክለትን/ የሚያስከትሉ ነገሮችን ማወቃቸውን ጥያቄ በመጠየቅ መከታተል፣
- የምግብ ብክለት ምን ችግር እንደሚያስከትል በመጠየቅ ግንዛቤያቸውን መገምገም፣
- የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎችን ለይተው ማወቃቸውን ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም፣

- ምግብን ለረጅም ጊዜ ሳይበላሽ ለማቆየት የሚረዱ ዘዴዎችን እንዲጠቅሱ መጠየቅ፣
- መልመጃዎችን መሥራታቸው ማረጋገጥ።

**የመልመጃ 1.1 መልሶች**

ሀ. 1. እውነት

4. እውነት

2. ሃሰት

5.

እውነት

3. ሃሰት

ለ. 1. ሀ

4. መ

2.ሐ

5. መ

3.ለ

ሐ. 1 ፦ ጣዕማቸው ይቀየራል፣

- መጥፎ ሽታ ያመጣሉ፣
- የመበስበስ ባህሪ ያሳያሉ፣
- እጅ እጅ ይላሉ፣

2. በዓይን የማይታዩ ጥቃቅን ህዋሣት እንደባክቴሪያ ያሉ ጀርሞች ናቸው

3. የተመጣጠነ ምግብ አራቱን የምግብ ክፍሎች ማለትም የሥጋ፣የወተት፣የእህልና ጥራጥሬና የአትክልትና ፍራፍሬ የምግብ ክፍሎችን ያካተተ ነው።

4. የተመጣጠነ ምግብ የመመገብ ጥቅም፣

- ሰውነትን ለመገንባትና ለመጠገን፣
- ሰውነትን ከበሽታ ለመከላከል፣
- ብርታትና ጥንካሬ ለማግኘት፣
- አጥንትንና ጥርስን ለማጠንከር ነው፣

5. የተለያዩ በሽታዎችን ያስከትላል።

ለምሳሌ፦ ኮሌራ፣ተውከት፣የደም ተቅማጥ፣አሜባ፣ጃርዲያ የአንጀት ተስቦ።

ሠንጠረዥ **1.2** የምግብ ዓይነትና የሚመደብበት የምግብ ክፍል

6.

| የምግብ ዓይነት | የምግብ ክፍል |
|---|---|
| ዳቦ | እህልና ጥራጥሬ |
| ብርቱካን፣ሎሚ፣ጐመን፣ሰላጣ፣ ቲማቲም | አትክልትና ፍራፍሬ |
| ስጋ | የሥጋ ክፍል |
| ወተት፣አይብ፣አሬራ፣ቅቤ | የወተት ክፍል |

## **1.2.** የቤተሰብ ጽዳት

የተመደበው ጊዜ **15** ክፍለ ጊዜ

**1.** ዝርዝር ዓላማዎች ይህን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የቤተሰብ ንፅህና ምን መምሰል እንዳለበት ያሳያሉ።
- የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ተግባራትን ያሳያሉ
- በጽዳት ጉድለት ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎችን ይገልፃሉ።
- የተመጣጠነ ምግብ ማለት የምንመገበው ምግብ አራቱን ክፍሎች መያዙ እንደሆነ ያስረዳሉ።
- ኤድስ በቤተሰቦቻቸውና በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሳቸው ተፅዕኖዎችን ይዘረዝራሉ።
- ከኤድስ ጋር አብረው ለሚኖሩ ሰዎች ምን ያህል ፍቅር እንደሚያሳዩ ይገልፃሉ።

**2.** ዝርዝር ይዘቶች፡-

- የቤተሰብ ጽዳትን ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአካባቢን ንፅህና መጠበቅ፣
- በጽዳት ጉድለት ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች፣
- ኤድስ በኛ ቤተሰብና በህብረተሰቡ ላይ ያለው ተፅእኖ።

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ከርዕሱ ቀጥሎ የቀረቡትን ቁልፍ ቃላት ያስተዋውቋቸው።

- ወደ ትምህርቱ ለመግባት የቤተሰብ ምንነት፣የቤተሰብ ጽዳትን መጠበቅ ጠቀሜታና የቤተሰብ ጽዳት ጉድለት ምን እንደሚያስከትል የሚሉትን የማነቃቂያ ጥያቄዎች በመጠየቅ ተማሪዎቹ የሚያቀርቡትን ሃሣብ ይቀበሉና ቤተሰብ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በጋራ የሚኖሩበት አባት፣ እናትና ልጆችን የሚያካትት ተቋም መሆኑን፣የቤተሰብ ጽዳት መጠበቅ ለቤተሰቡ ጤና አስፈላጊ መሆኑንና የቤተሰብ ጽዳት ጉድለት ደግሞ ለተለያዩ በሽታዎች እንደሚያጋልጥ ያስረዷቸው።
- እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የግል ጽዳቱን በሚገባ መጠበቅ እንዳለበት፣የግል ንፅህና መጠበቅ ማለት የቤተሰቡ ንፅህና መጠበቅ እንደሆነ ያስረዷቸው።
- የቤተሰብ ጽዳትን መጠበቅ ተግባራዊ ለማድረግ ቀጥሎ በዝርዝር የቀረቡትን መንገዶች መከተልና ማወቅ እንደሚገባ ያስገንዝቧቸው። እነዚህም፡-
    1. የመኖሪያ ቤት በርና መስኮቶችን በመክፈት ንፁህ አየር ገብቶ እንዲዘወርና መልካም ጠረን እንዲኖር ማድረግ ፣
    2. የግልና የቤተሰብ ልብስ ንፅህና መጠበቅ፣
    3. ቤትንና የመኖሪያ ግቢን ማፅዳት፣
    4. የቤት ዕቃዎችን /የምግብ ማብሰያና መመገቢያ ዕቃዎችን/በንፅህና መጠበቅ፣
    5. የሽንት ቤትን /መፀዳጃ ቤትን/መጠቀም አስፈላጊ መሆኑ፣
    6. በግቢ ውስጥና ከግቢ ውጭ አካባቢ የሚገኙትን ቆሻሻዎች ማፅዳት የሚሉ ናቸው።
- እነዚህን ነጥቦች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በዝርዝር በተገለጸው መሠረት ትኩረት ሰጥተው ተማሪዎችን አሳትፎ በመወያየት ትምህርቱን እንዲጨብጡ ይርዷቸው።
- የልብስ ንፅህናን መጠበቅ በተመለከተ ቤተሰቡን ከተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል፡-
    - የቀን ልብሶችን፣
    - የሌሊት ልብሶችን፣
    - የውሰጥ ልብሶችን በየጊዜው ማጠብ እንደሚገባ ያስረዷቸው
- የመኖሪያ ቤትንና ግቢን በየቀኑ መጥረግና ማፅዳት ከተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል የሚያስችል መሆኑን ያስገንዝቧቸው።

- የቤት ዕቃዎችን ማለትም የማብሰያ፣የማቅረቢያና የመመገቢያ ዕቃዎችን በውሃና በሳሙና በማጠብ ንፅህና መጠበቅ እንደሚገባ ያስረዷቸው።
- የመጸዳጃ ቤት መጠቀምን ልምድ ማዳበር ተገቢ መሆኑን፣ከሽንት ቤት ውጭ በሚደረግ የአይነ ምድር መፀዳዳት ምክንያት እንደ አሜባ፣የአንጀት ተስቦ፣ኮሌራና ሌሎችም ተላላፊ በሽታዎች በዝንቦች አማካይነት ሊተላለፉ እንደሚችሉ ማስረዳት
- የአካባቢ ንፅህናን ለመጠበቅ ምን ምን ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚገባ ተማሪዎችን ተራ በተራ በመጠየቅ ሙከራቸውን መቀበልና የሚሰጧቸውን ሃሣቦች ቀጥሎ ከተገለፁት አካባቢን የማፅዳት ዘዴዎች ጋር እያዛመዱ በመዘርዘር ያስረዷቸው።

እነዚህም፡- ደረቅ ቆሻሻዎችን ሰብስቦ በተዘጋጀ ጉድጓድ ውስጥ መጣልና

ማቃጠል፣

- የዝንቦች መራቢያ ቆሻሻ ቦታዎችን ማስወገድ፣
- በየሜዳው መፀዳዳትን ማስወገድ በዓይነ ምድር ላይ የሚራቡትን ነፍሳት ያስወግዳል።
- የወባ መራቢያ ቦታን፣የረጋና የተጠራቀመ ውሃን፣ መጥረግና ማድረቅ የሚሉት ናቸው።

ስለዚህ ተማሪዎቹ በአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ትምህርት ያገኙትን ዕውቀት በተግባር እንዲተረጉሙ በትምህርት ቤትና በአካባቢ ጽዳት ተግባር እንዲሳተፉ ይገፋፏቸው። ለመጠጥና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል ውሃ ንፅህናው የተጠበቀ መሆን አለበት። ውሃን ከተለያዩ ቦታዎች ማለትም ከኩሬ፣ከወንዝና ከሐይቅ እናገኛለን። ከነዚህ ቦታዎች የተቀዳው ውሃ ከመጠጣቱ በፊት ንፅህናውን የጠበቀ እንዲሆን ምን ማድረግ እንዳለብን ይጠይቋቸውና ሃሣባቸውን ይቀበሏቸው። ከዚህያም በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ውሃን ንፁህ የማድረግ ዘዴዎች፡-

- ውሃን አፍልቶና አቀዝቅዞ መጠጣት፣
- ውሃን ማጥለል፣
- ውሃን ንፁህ የሚያደርጉ ኬሚካሎችን እንደ ውሃ አጋር የመሳሰሉትን ባለሙያዎችን አማክሮ መጠቀም
- ውሃን ማጣራት የሚሉትን በዝርዝር በማስረዳት ተማሪዎቹም የቀሰሙትን እውቀት በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው።

- ተግባራዊ ክንዋኔዎችን በሚመለከት በአካበቢያቸው ረግቶ የተቀመጠ ወይም የፍሳሽ ማስወገጃ የተዘጋበትና የተጠራቀመ ቆሻሻ ውሃ ምን ችግር እንደሚያስከትልና እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል በቡድን ሆነው እንዲወያዩና የመፍትሔ ሃሣብ እንዲያቀርቡ የቤት ሥራ ወይም የክፍል ሥራ አድርገው ይስጧቸው። በቡድን የተወያዩበትን ሃሣብም ይቀበሏቸውና የፍሳሽ መውረጃ የተዘጋበትና ረግቶ የተቀመጠ ውሃ የሚያመጣው ጉዳት የወባ በሽታን የሚያስተላልፉ ትንኞች የሚያራቡና የወባ በሽታ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚያዛምቱ መሆኑን እንዲረዱ ያድርጓቸው።

- ይህን የተጠራቀመና ለወባ በሽታ መዛመት ምክንያት የሆነው ውሃ የማስወገጃ ቦይን በመክፈት እንዲወገድና አካባቢውን ደረቅ በማድረግ ችግሩን ለማስወገድ እንደሚቻል ያስረዷቸው።

- በአካባቢያቸው የተጠራቀመ ውሃ ወደሚገኝበት ቦታ በመሄድ የፍሳሽ ማስወገጃ የተዘጉ የውሃ መውረጃ ቦዮችን በመክፈትና በማስወገድ ሥራ እንዲሳተፉና ልምድ እንዲያዳብሩ ያስገንዝቧቸው። ስላከናወኑት ተግባር ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል ሪፖርት እንዲያደርጉም ይዘዟቸው።

- የውሃ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችና የዝናብ ውሃ መቀበያና ማጠራቀሚያ ዕቃዎችን እንዴት በንፅህና መያዝ እንደሚገባ  እንዲወያዩ ማድረግ። ለብዙ ጊዜ የተጠራቀመ ውሃን በማስወገድና እቃዎቹን በየጊዜው በማጠብ የውሃውንና የዕቃዎቹን ንፅህና መጠበቅ እንደሚቻል አስረድቶ ማለፍ።

- በአካባቢያቸው በጽዳት ጉድለት /በተበላሸ ውሃ/ ምክንያት የተከሰቱ በሽታዎችን ስም እንዲናገሩ መጠየቅና የሚሰጡትን ሃሣብ ተመርኩዘው የተበላሸ ወይም ንፅህና የጐደለው ውሃ ለተላላፊ በሽታዎች እንደሚያጋልጥ ማስገንዘብ መልካም ነው።

- ንፅህና በጐደለው ውሃ የሚተላለፉ በሽታዎችም እንደ ታይፎይድ፣ኮሌራ፣ ተስቦና አሜባ መሆናቸውን ማስረዳት፣የውሃን ንፅህና ለመጠበቅ በውሃ አካባቢ ዓይነ ምድርን መፀዳዳት እንዳይኖር ማወቅ እንደሚገባና በተደራጀ ንፅህናው በተጠበቀና የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ያለው የመፀዳጃ ቤት መጠቀም ዓይነ ምድር በጉድጓዱ ውስጥ እንዲጠራቀም ለማድረግ እንደሚረዳ ያስረዷቸው።

- በዚህም መሠረት የተሻለ ሽንት ቤትን ለመሥራት ምን ማድረግና የሚያስፈልጉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ እንዲዘረዝሩ ተማሪዎችን መጠየቅና በመማሪያ መጽሐፉ የተገለፀውን መሠረት በማድረግ የተሻሻለ የሽንት ቤት አሠራርን ይግለጹላቸው።

- ኤድስ በቤተሰብና በህብረተሰብ ላይ ያለው ተፅዕኖን በሚመለከት የኤች አይ ቪ ኤድስን በሽታ ሰውን እንዴት እንደሚያጠቃ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። የሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅምን የሚያዳክምና ለሌሎች በሽታዎች እንደሚያጋልጥ ያብራሩላቸው።

- የኤድስ መተላለፊያ መንገዶቹን በክፍል ውስጥ ፈቃደኛ በሆነ ተማሪ እንዲነበብ ያድርጉ። ከዚያም በያንዳንዱ መተላለፊያ መንገድ ላይ ማብራሪያ ይስጧቸው።

- ኤች አይ ቪ ኤድስ በቤተሰብና በህብረተሰብ ላይ ምን ተፅዕኖ እንደሚያደርስ ተማሪዎቹን ያወያዩአቸው።

ከዚያም - ምርታማነትን እንደሚቀንስ፣

- የገቢ ምንጭን እንደሚቀንስ፣
- የጤናና የትምህርት አገልግሎቶችን እንደሚቀንስ፣
- በበሽታው ምክንያት ወላጅ የሚያጡ ህፃናት ቁጥር እንደሚጨምር በማስረዳትና ከኤድስ ጋር አብረው ለሚኖሩ ሰዎች የተለየ እንክብካቤ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ በመግለጽ ትምህርቱን ያጠናቅቁ

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የግል የቤተሰብና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅን የሚያሳዩ ሥዕሎችና ፖስተሮች፣
- የግልና የአካባቢ ንፅህና የሚያጓድሉ ነገሮችን የሚያሳዩ ሥዕሎች፣
- በመፀዳጃ ቤት መጠቀም ለጤንነት ዋስትና መሆኑን የሚያሳዩ ሥዕሎች
- የመጠጥ ውሃ ንፅህናው የተጠበቀ መሆን እንዳለበት የሚያሳይ ሥዕል።

## 5. የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- የግልና የቤተሰብ ጽዳት አጠባበቅ ምንነትና ጠቀሜታን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣
- የቤተሰብ ንፅህና/ጽዳት/ አጠባበቅ ዘዴዎች ማወቃቸውን ማረጋገጥ፣
- የአካባቢ ንፅህናን የሚያጓድሉ ሁኔታዎችን በመጠየቅ መገምገም፣
- የአካባቢ ጽዳትን አጠባበቅ መለማመዳቸውን መገምገም፣
- ውሃን ንፁህ የማድረጊያ ዘዴዎችን እንዲጠቅሱ መጠየቅ፣

- ንፅህናው በተጓደለ ውሃ አማካይነት የሚከሰቱ በሽታዎችን መረዳታቸውንና ማብራራት መቻላቸውን መገምገም፣
- የኤድስ ህመም በቤተሰብና በአካባቢ ህብረተሰብ ላይ የሚያስከትለውን ችግር ለይተው እንዲናገሩ ማድረግ፣
- ከኤድስ ጋር አብረው ለሚኖሩ ሰዎች ያላቸውን ፍቅርና እንክብካቤ ምን እንደሚመስል ማረጋገጥ፣
- መልመጃዎችን ሁሉ መሥራታቸውን ማረጋገጥ።

- የመልመጃ **1.2** መልሶች

ሀ. 1. እውነት 4. ሀሰት

2. እውነት 5. እውነት

3. ሀሰት

ለ. 1.መ 4. ሐ

2. መ 5. ሀ

3. መ

## **1.3** የእረፍት ጊዜና መዝናናት

የተመደበው ጊዜ **10** ክፍለ ጊዜ

**1.** ዝርዝር ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- የእረፍት ጊዜና የመዝናናትን ጥቅም ይናገራሉ።
- የእረፍት ጊዜያቸውን በተገቢው መልኩ ለመጠቀም ይችላሉ።
- በእረፍትና በመዝናናት የታገዘ ሥራ ውጤታማ መሆኑን ይገልፃሉ።
- በሚሠሩት ሥራ መካከል እረፍት ማድረግን ይለማመዳሉ።

**2.** ዝርዝር ይዘቶች፡-

- የተመጣጠነ የእረፍት ጊዜና መዝናናት፣
- የእረፍትና የመዝናኛ ጊዜን በተገቢው መጠቀም፣
- የትርፍ ጊዜና የመዝናናት ዓይነቶች፣

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች፡-

- ወደ ዝርዝር ትምህርት ውስጥ ከመግባትዎ በፊት ከዋናው ርዕስ ሥር የተጠቀሱትን ቁልፍ ቃላት ለተማሪዎቹ ያስተዋውቋቸው።
- የተመጣጠነ የእረፍት ጊዜና መዝናናት የሚለውን ርዕስ ሲጀምሩ የእረፍት ጊዜና የመዝናናት ጥቅም ምን እንደሆነ በማነቃቂያነት የቀረበውን ጥያቄ ይጠየቋቸው። ሃሣቦቻቸውን ይቀበሉ። ከዚያም የመዝናኛ ጊዜ መኖር በሥራ ለደከመ ሰውነትና አእምሮ በጣም አስፈላጊ መሆኑንና ለሚቀጥለው ሥራችን በአዲስ መንፈስና ፍላጐት እንድንሠራ የሚረዳን መሆኑን ያስረዷቸው።
- ሥራ መሥራት የህይወት መሠረት መሆኑን፣ሥራ መስራትም ለመኖር የሚያስችለን መሠረታዊ ፍላጐቶቻችንን ለማሟላት ገቢ እንደሚያስገኝልን በማብራራት ይግለጹላቸው። ሥራ ስንሠራ ግን በየመሐሉ የዕረፍት ጊዜ ሊኖር እንደሚገባ ያሳውቋቸው። መሠረታዊ ፍላጐቶች የሚባሉትም ለሰው ልጅ መኖር አስፈላጊ የሆኑት ምግብ፣መጠለያና ልብስ መሆናቸውን ያስረዷቸው።

- ሥራን በአቅድና በቅደም ተከተል መምራት እንደሚገባ፣ ተማሪዎችም የሚሠሩትን ሥራ በቅደም ተከተል ለማከናወን በሚከተለው ሁኔታ ከፋፍሎ መሥራት ጠቃሚ መሆኑን ይገልጹላቸው።

እነዚህም፡- 1. ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት፣

2. በትምህርት ቤት ውስጥና

3. ከትምህርት ቤት መልስ የሚሉ ናቸው።

- ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት መዘጋጀት ፣ ማለትም፡ መፀዳጃ ቤት ሄዶ መፀዳዳት ፣ እጅና ፊትን መታጠብና ቁርስ መብላት እንደሚያስፈልግ መንገር፣

- በትምህርት ቤት ውስጥ የትምህርት ሰዓትን አክብሮ መማር የዕረፍት፣ ሰዓትን በሚገባ መጠቀም ኳስ መጫወት፣ግቢን መጐብኘት፣ ከጓደኛ ጋር መወያየትና ሌሎችንም እንደፍላጐታቸው ማድረግ እንደሚገባ፣

- ከትምህርት ቤት መልስም ለተወሰነ ጊዜ እረፍት ማድረግና መዝናናት ከዚያም ማጥናት፣ቤተሰብን በሥራ መርዳት እንደሚያስፈልግ ያብራሩላቸው።

- በአንድ ቀን ውስጥ የሚከናወኑ ሥራዎች ሊበዙ እንደሚችሉና ሁሉንም በአንድ ጊዜ መሥራት እንደማይቻል ማስረዳት፣

- ያለማቋረጥ ሥራ መሥራትም በሥራ ብዛት ምክንያት የሰውነት ድካምን እንደሚያስከትል ነገር ግን ሥራን በሰዓታት ከፋፍሎ በየመካከሉ ዕረፍት በመውሰድ መሥራት ውጤታማ እንደሚያደርግ ያስረዷቸው። ሰውነትን እያሳረፉና እያዝናኑ ሥራን መሥራት ሰውነታችን በቀላሉ በበሽታ እንዳይጠቃ እንደሚረዳ በተጨማሪም የእረፍት ጊዜ መኖር ከቤተሰቦቻችንና ከጓደኞቻችን ጋር ለመገናኘት፣ ጊዜ ሰጥተን ለመወያየትና ለመጫወት እንደሚጠቅመን ያብራሩላቸው።

- የተመጣጠነ የእረፍትና የመዝናኛ ጊዜ ሳንጠቀም ቀኑን ሙሉ በሥራ ላይ ብቻ የምንጠመድ ከሆነ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች እንደሚገጥሙን ማስረዳት

እነሱም፡- - የድካም ስሜት ፣

- የሥራ ፍላጐት መቀነስ፣
- ሰውነት በቀላሉ በበሽታ መጠቃት፣

- ከቤተሰብና ከጓደኞች ጋር የመገናኛ ጊዜ ማጣት ናቸው።

- የእረፍትና የመዝናኛ ጊዜን በተገቢው መጠቀም የሚለውን ርዕስ ከመጀመርዎ በፊት ተማሪዎቹ የእረፍት ጊዜያቸውን ምን በመስራት እንደሚያሳልፉ ተሞክሮ ካላቸው ለክፍል ጓደኞቻቸው ዘርዝረው እንዲናገሩ ይጠይቋቸውና የእረፍት ጊዜን እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ማሳለፍ እንደሚቻል ቀጥሎ በተገለጸው መሠረት ያሳውቋቸው።
- በአንዳንድ አካባቢ የሚኖሩ ተማሪዎች የእረፍት ጊዜአቸውን፡-
  - በቤተመጻሕፍት ውስጥ መጽሐፍን በማንበብ፣
  - ጋዜጣና መጽሔትን በማንበብ፣
  - ከጓደኞቻቸው ጋር ስለትምህርት በመወያየት፣
  - ስለ አካባቢያቸው ተፈጥሮአዊ ገጽታ ጠይቆ በማወቅ፣
  - ልዩ ልዩ ሥፍራዎችን በመጎብኘት፡-
    - ፓርኮችን በመጐብኘትና ተፈጥሮን በማድነቅ፣
    - ሙዚየሞችን በመጐብኘት፣
    - ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶችን በመጐብኘትና በማስተዋል። የእረፍት ጊዜያቸውን እንደሚያሳልፉ ዘርዝረው በማስረዳት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ካሉት ሥዕሎች ጋር እንዲያገናዝቡ ይርዷቸው።
- በሌላ አካባቢ ያሉ ተማሪዎች ደግሞ የእረፍት ጊዜያቸውን ስፖርት ማዘውተሪያ በመሄድ ልዩ ልዩ ስፖርቶችን በመሥራት ኳስ በመጫወት፣ሩጫ በመወዳደር እንደሚያሳልፉ ከላይ ከቀረቡት ጋር በማስተያየት ያስተምሯቸው
- ልዩ ልዩ ቅርፃ ቅርፆችንና እጅ ሥራዎችን በመሥራት፣
- ቴሌቪዥን በማየት፣ሬዲዮን በማዳመጥና ጋዜጣን በማንበብ አዳዲስ ሃሣቦችን በማወቅ እንደሚያሳልፉ ያስረዷቸው። በተጨማሪም ተማሪዎች ከላይ ከተጠቀሱት የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያዎች ውስጥ የትኞቹን በማከናወን እንደሚያሳልፉ ይጠይቋቸውና አወያይተው ትምህርቱን ያጠናቁ።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-

- ተማሪዎች በቤተ መጻሕፍት ወይም በቤት ውስጥ ጥናት ላይ እንዳሉ የሚያሳይ ሥዕል፣
- በእረፍት ጊዜ ልዩ ልዩ ሥፍራዎችን መጐብኘት፣
- ልዩ ልዩ የእጅ ሥራዎችን መሥራት፣

**5.** የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- የእረፍት ጊዜና የመዝናናት ጥቅም መረዳታቸውን መገምገም
- ሥራን እረፍት እየወሰዱ መሥራት ለምን እንደሚጠቅም መጠየቅ
- ተማሪዎች የዕረፍት ጊዜያቸውን ምን በማከናወን እንደሚያሳልፉ መጠየቅ

የመልመጃ **1.3** መልሶች

ሀ.

1. ሃሰት

2. ሃሰት

3. እውነት

4. እውነት

ለ. **1.** በሥራ የደከመውን ሰውነታችን ለተወሰነ ጊዜ እረፍት እንዲወስድ ለማድረግ

- የሚቀጥለውን ሥራ በአዲስ መንፈስና በፍላጐት ለመሥራት እንድንችል

**2.** ድካም ይሰማቸዋል

- የሥራ ፍላጎታቸው ይቀንሳል።
- ሰውነታቸው በቀላሉ በበሽታ ይጠቃል
- ከጓደኞቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የመገናኛ ጊዜ ያጥራቸዋል።

**3.** ይህ ጥያቄ በተማሪዎቹ ፍላጎት የሚወሰን ይሆናል።

**4.** ታሪካዊ ሥፍራዎችን መጎብኘት ማለትም፡-

  - ፓርኮችን፣
  - ሙዚየሞችን፣
  - ቅርሶችን።

- በቤተ መጻሕፍት መጻሕፍትን ማንበብ።
- በህብረት ስለተማሩት ትምህርት መወያየትና ሌሎችም ናቸው።

## የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

ሀ. 1. ሃሰት 5. ሃሰት

2. እውነት 6. እውነት

3. ሃሰት 7. እውነት

4. እውነት

ለ. 1. መ 4. ለ

2. መ 5. መ

3. መ 6. መ

ሐ. 1. ፓስቸራይዜሽን

2. በእህልና ጥራጥሬ

3. የወተት ምግብ ክፍሎች

4. እረፍት ማድረግ

5. የኤድስ በሽታ

መ. እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በሚሰጡት መልስ ይወሰናሉ። ቤተሰባቸው ያከናወነው ከሆነ

አዎ፦ ያላከናወነው ከሆነ አይደለም ብለው እንዲመልሱ መጠየቅ ይገባል።

ሠ. 1. የተመጣጠነ ምግብ ምንጭ የሆኑትን ምግቦች መመገብ

2. ምግብንና የመጠጥ ውሃን ከሚበክሉና በሽታ ከሚያስከትሉ ነገሮች ሁሉ መከላከልና በንፅህናና በጥንቃቄ መያዝ

3. የወተት ክፍል፣የሥጋ ክፍል የአትክልትና ፍራፍሬ ክፍልና የእህልና ጥራጥሬ ምግብ ክፍሎች ናቸው

4. 1. የግል ንፅህና ጉድለት

2. ጥቃቅን ተህዋስያን /ጀርሞች/

3. የምግብ መሥሪያና መመገቢያ ዕቃዎች ንፅህና ጉድለት

4. የንፁህ ውሃ አለመጠቀም እና ሌሎችም ናቸው።

5. - የምግብ ማዘጋጃ ዕቃዎችን ማጠብ

- አትክልትና ፍራፍሬን አጥቦ መመገብ
- ለምግብ ዝግጅት የሚሆን ንፁህ ውሃን መጠቀም
- እጆቻችንና ጥፍሮቻችንን ማፅዳትና ሌሎችም ናቸው

6. ዝንብ፣ትንኝ፡በረሮዎች

7. - ልቅ የሆነ የግብረስጋ ግንኙነት

- የደም ንክኪ
- ከነፍሰጡር እናት ወደ ህፃኑ በወሊድ ጊዜ

8. - የድካም ስሜት

- የሥራ ፍላጎት መቀነስ
- ሰውነት በቀላሉ በበሽታ መጠቃትና ሌሎችም ናቸው

9. ልዩ ልዩ ሥፍራዎችን በጋራ መጎብኘት

- ፓርኮችን
- ሙዚየሞችን
- ቅርሶችን

- ተፈጥሮአዊ ቦታዎችን

# ክፍል ትምህርት ሁለት

# ተፈጥሮአዊ አካባቢያችን

የተመደበው ጊዜ **68** ክፍለ ጊዜ

*መግቢያ*

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተፈጥሮ ሀብት፣ኃይልና ጉልበት የሚሉት ናቸው። በዚህ ደረጃ ያሉትን ተማሪዎች አስፈላጊውን እውቀት ለማስጨበጥ እንዲቻል የትምህርቱ አሰጣጥ በተግባር ላይ ያተኮረና አሳታፊ በሆነ መንገድ ለማቅረብ ተሞክሮአል። በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ በውይይት ላይ ተመርኩዘው ያላቸውን ተሞክሮ እየተለዋወጡ እርስዎም ከሚሰጡት ትምህርት ጋር እያዋሃዱ እንዲማሩ የበኩልዎን ጥረት ያክሉበት።

በማስተማሪያው መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎችን እየተገበሩ የራስዎንም በማከል በመማሪያው ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎች በክፍል ሥራና በቤት ሥራ መልክ እየሰጡ ትምህርቱን እንዲያስተላልፉ ይጠበቃል።

አጠቃላይ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ፦

- አፈር፣ውሃ፣አየር፣ደንና የዱር እንስሳት የተፈጥሮ ሀብቶች መሆናቸውን ይገልፃሉ።
- ተፈጥሮን ያደንቃሉ።
- ሙቀት፣ብርሃንና ድምፅ የኃይል ዓይነቶች እንደሆኑ ይገልፃሉ፣ቀላል ተግባራዊ ክንዋኔዎችን በማድረግም ውጤቶቻቸውን ያሳያሉ።
- የቀላል መሣሪያዎችን አገልግሎትና እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ይለያሉ።
- በመማር ሂደት ውስጥ ሳይንሳዊ ክህሎቶችን ያሳያሉ፤አካባቢን ማጥናትን ፣መመዝገብን፣መመደብን፣መጠየቅን፣መለካትንትርጉምመስጠትን፣ ማጠቃለልን፣ ግንኙነት መፍጠርንና በጋራ መሥራትን ይለማመዳሉ።

# 2.1 የተፈጥሮ ሀብት

የተመደበው ጊዜ **25** ክፍለ ጊዜ

## 1. ዝርዝር ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ፡-

- አፈር የተፈጥሮ ሀብት እንደሆነ፣ የአፈር ዓይነቱን፣ ጥቅሙንና ሊደረግለት የሚገባውን ጥበቃ ያብራራሉ።
- ውሃ የተፈጥሮ ሀብት መሆኑን፣የውሃን ጥቅም፣ ውሃን በአግባቡ መጠቀምና ሊደረግለት የሚገባውን እንክብካቤ ያስረዳሉ።
- አየር የተፈጥሮ ሀብት መሆኑን፣ጥቅሙንና እንዲሁም በአየር ላይ የሚደርሰውን ብክለት ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ዘዴዎችን ይዘረዝራሉ።
- ደን የተፈጥሮ ሀብት መሆኑን፣ የደንን ጥቅምና ሊደረግለት የሚገባውን ጥበቃ ይገልፃሉ።
- የዱር እንስሳት የተፈጥሮ ሀብቶች መሆናቸውን፣ የሚሰጡትን ጥቅምና ሊደረግላቸው የሚገባውን ጥበቃ ያብራራሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች፡-

- አፈር
- ውሃ
- አየር
- ደን
- የዱር እንስሳት

## 3. የመማር - ማስተማር ክንውኖች ፡-

መምህር፣የተፈጥሮ ሀብቶች የሚለውን ርእስ ሲያስተምሩ በማነቃቂያ ጥያቄ ወይም ተግባር መክፈቻ ጥያቄ ይጀምሩ። ተማሪዎች ካላቸው የእውቀት እርሾ በመነሳት ወደ ውይይት እንዲገቡ መምራት ይጠበቅብዎታል። ተማሪዎች በቡድንም ሆነ በተናጠል ተወያይተው ሲያበቁ የደረሱበትን ማጠቃለያ መሠረት በማድረግ ተጨማሪ ማብራሪያም ይስጧቸው። በዚሁ መሠረት አፈር የአፈር

ቅንጣቶችን መሠረት ባደረገ አመዳደብ በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚመደብ፣የአፈሮቹን ዓይነትና እንዲሁም ባህሪይ ያብራሩላቸው።

ተማሪዎች ለውይይት የአፈር ናሙና ማግኘት ባይችሉ እርስዎ ሊያስተባብሩላቸው ይገባል።

ሠንጠረዥ 2.1 የአፈር ዓይነቶች

| ተ.ቁ | የአፈሩ ዓይነት | የአፈሩ ቅንጣት መጠን በሚሊሜትር | የአፈሩ በሀርይ |
|---|---|---|---|
| 1 | አሸዋ አፈር | 0.2 እስከ 2 | ውሀ ቶሎ ይመጣል/ያስተላልፋል/ቶሎ ይደርቃል |
| 2 | የሸክላ አፈር | 0.002 በታች | ቶሎ አይርስም፣ውሃ ይቋጥራል |
| 3 | ዋልካ አፈር | 0.002 እስከ 2 | የተለያዩ አፈር ቅንጣቶችን ይይዛል። የሚርሰውም፣የሚደርቀውም በመካከለኛ ፍጥነት ነው። |

ተማሪዎች በቡድን ሆነው በሚወያዩበት ጊዜ የአፈሮቹን ባህርያት እንዲዘረዝሩና እንዲመዘግቡ ይምሯቸው።

ተማሪዎች ስለ አፈር ጥቅም የሚያውቁትን ሁሉ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። ከውይይታቸውም በኋላ አፈር፡-

- አዝርእትን ለማምረት/ለእርሻ ሥራ/እንደሚጠቅም፣
- ለግንባታ ሥራ /ለቤት፣ለመንገድ ወዘተ/
- ህይወት ያላቸው ነገሮች መጠለያ መሆኑን ጨምረው ያብራሩላቸው።

ቀጥሎም ለአፈር ጥበቃ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ላይ እንዲወያዩ ይምሯቸው። በውይይታቸው ወቅትም አፈር በጐርፍ፣ በወንዞችና በንፋስ ተጠርጐ እንዳይሄድ ምን ምን ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው እንዲዘረዝሩ መጠቆም ያስፈልግዎታል። ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን ከቋጩ በኋላ የቀረ ሊኖር ስለሚችል ሌላም አክለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተዘረዘሩትን ዘዴዎች ይንገሯቸው።

ውሃን በተመለከተም በማነቃቂያ ጥያቄ ይጀምሩላቸው። ቀጥለውም ውሃ ከየት እንደሚገኝ፣ በተማሪዎቹ አካባቢ የውሃ አጠቃቀም እንዴት እንደሆነ አንስተው በዝርዝር እንዲወያዩባቸው ይምሯቸው። ውሃ ለምን ለምን እንደሚያገለግል እንዲያብራሩ ይጠይቋቸው። ውሃ የህይወት መገኛ መሆኑን፣በቤት ውስጥ ለምግብ ማብሰያ፣ ለመጠጥ፣ለመታጠቢያ ወዘተ ማገልገሉንና የምንጠቀምባቸው እንስሳትም ውሃ

እንደሚያስፈልጋቸው፣ ውሃ ለግብርና ሥራ /ሰብል ለማምረት/ ለኢንዱስትሪና ኃይል ማመንጫ አገልግሎት እንደሚሰጥ ወዘተ ማጠቃለያ ላይ መድረሳቸውን ያረጋግጡ።

ቀጥሎም ውሃን ማቆሸሽ የሚችሉ ነገሮች ከአካባቢያቸው በመነሳት እንዲናገሩ ያድርጓቸው። ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን ከቋጩ በኋላ የቀረ ሀሳብ ሊኖር ስለሚችል የተወያዩባቸውን በማስተካከልና ያልጠቀሱትን በማከል ውሃን ከብክለት ለመታደግ አስፈላጊ የሆኑ ዘዴዎችን ጨምረው እንዲወያዩባቸው ፍንጭ ይስጡዋቸው።

በተጨማሪም ውሃ እንዴት ሊባክን እንደሚችል ማወያየትና ውሃን በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ሊያሰምሩበት ይገባል። የውሃ እጥረት ባለበት አካባቢ ቆሻሻ ውሃን አጣርቶና አፍልቶ መጠቀም እንደሚገባም ይግለፁላቸው።

አየር ሌላው የተፈጥሮ ሀብት ነው። ስለ አየር ለማስተማር እንደተለመደው በማነቃቂያ ጥያቄ ይጀምሩ። ተማሪዎቹ ሳይተነፍሱ ለምን ያህል ሊቆዩ እንደሚችሉ በተግባር እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው። ራሳቸው ማጠቃለያ ላይ እንዲደርሱ ያበረታቷቸው። በመቀጠልም የአየርን ጥቅሞች በቡድን ሆነው እንዲዘረዝሩ ያመቻቹ። በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተገለፀውን ሠንጠረዥ 2.2 መሠረት በማድረግ አየር የሚበከልባቸውን አጋጣሚዎች እንዲዘረዝሩ ያድርጉ። ተማሪዎቹ አየር ይበልጥ የሚበከለው ሰው ሰራሽ በሆኑ ነገሮች መሆኑን ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ይምሯቸው። አየርን ከብክለት ለመከላከል፦

- በተማሪዎቹ ደረጃ ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎችን እንዲዘረዝሩ ይጠይቋቸው።
- በአካባቢና በመንግሥት ደረጃ ሊወሰዱ ይገባል የሚሉትን እርምጃዎች የሚችሉትን ያህል ሀሳብ እንዲሰጡ ያበረታቱዋቸው። በመጨረሻም ዋና ዋና ነጥቦችን በማንሳት ያጠቃሉላቸው።

ስለ ደን ሲያስተምሩ ስለምንነቱ በመጠየቅ ይጀምሩ። ተማሪዎች ስለ ደን ያላቸውን ግንዛቤ ከአሰባሰቡ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተገለፀውን ይጥቀሱላቸዉ። ከዚያም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያለውን ሥዕል 2.3 ን መሠረት በማድረግ ተማሪዎቹ ስለደን ጥቅም እንዲዘረዘሩ ይርዷቸው።

ተማሪዎቹ ደን በአካባቢያቸው፣በክልላቸውና በሀገራቸው እየተመናመነ መሄዱን እንዲገነዘቡ ያድርጉ። ከዚህ በመነሳትም የደን ሀብታችንን ቢያንስ ባለበት ሁኔታ መጠበቅና ማቆየት ሲሆን ደግሞ ማልማት እንደሚገባም ተማሪዎች እንዲረዱ ያድርጓቸው።

ደን እንዲመናመን ከሚያደርጉ ነገሮች የሚያውቁትን ያህል እንዲዘረዝሩ ይጠይቋቸው። ከዚህም በመቀጠል የደን መመናመን ያስከተላቸውን ችግሮች ጨምረው እንዲወያዩ ያበረታቷቸው። ሀሳባቸውን ከቋጩ በኋላ የደን መመናመን ካስከተላቸው ችግሮች ውስጥ እንዳንዶቹ፦

- የአየር ንብረት ለውጥ /ድርቅ/፣

- የሙቀት መጨመር፣
- የውሃ እጥረት፣
- የአፈር በጎርፍና በወንዝ መሸርሸር፣
- የዱር እንሰሳት መሰደድ፣
- ከደን የሚገኝ ጥቅም መጓደል የመሳሰሉትን ይጥቀሱላቸው።

በመጨረሻም ለደን መደረግ ያለበት ጥበቃ አንድ በአንድ በዝርዝር እንዲገነዘቡ ይርዷቸው።

ተማሪዎቹ የዱር እንስሳትን የተለያዩ ስሞች /የሚያውቁትን/ እንዲጠሩ ያበረታቷቸው። ከዚያም ስሞቹ ተመዝግበው እንዲቀመጡ ያድርጉ። ከተጠቀሱት የዱር እንስሳት ውስጥ በአረባባቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው፣ በአመጋገባቸውና በአኗኗራቸው የሚኖራቸውን ልዩነትና አንድነት እንዲያመዛዝኑ ያበረታቷቸው።

የዱር እንስሳት ቁጥር እየተመናመነ መሆኑን እንዲረዱና የመቆርቆር ስሜት እንዲያድርባቸው መቀስቀስ ይጠበቅብዎታል።

የዱር እንስሳት መኖር ለአንድ ሀገር ህዝብ ያለውን ጠቀሜታ በዝርዝር እንዲናገሩና ከዚህ አንፃር ለዱር እንስሳት ጥበቃ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች አንድ በአንድ እንዲዘረዝሩ ይርዷቸው።

## 5. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- በአካባቢው ፓርክ ካለ ማስጐብኘት፣
- የእርከን አስተራረስ ዘዴ የሚያሳይ ሥዕል፣
- የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች የዛፍ ችግኝ ሲተክሉ የሚያሳይ ሥዕል፣
- የውሃ ብክለትን የሚያሳይ ሥዕል፣
- የአየርን መበከል የሚያሳይ ሥዕል፣
- የዱር እንሰሳትን የሚያሳይ ሥዕል፣
- በአካባቢው የአፈር ጥበቃ ሥራ ካለ ወስዶ ማሳየት።

እነዚህን ሥዕሎችና ሌሎችንም ከመማሪያ መጽሐፍ በመውሰድ አሳድገው ሊጠቀሙ ይችላሉ። ከተቻለ ከአቅራቢያ ከሚገኝ የግብርና መሥሪያ ቤት ፖስተሮችን ወስዶ ማስተማር ይችላሉ።

ከዚህም በላይ ባለሙያውን ወደ ክፍል ጋብዞ ታዳሽ ስለሆኑት የተፈጥሮ ሀብቶች ማለትም ስለ አፈር፣ውሃ፣አየር፣ደንና የዱር እንሰሳት ማስተማር የበለጠ ተጨባጭ ትምህርት እንዲሰጥ ያደርገዋል።

እንደዚሁም በት/ቤቱ አካባቢ ከሚገኙት ጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮችና የግብርና ጽህፈት ቤቶች ስለ እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠባበቅ ባለሙያ ጋብዞ ትምህርቱ እንዲሰጥ ማድረግ ይችላሉ።

## 6. የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎች

መምህር! ይዘት 2.1 ሥር የተዘረዘሩትን ፍሬ ሃሣቦች ተማሪዎች ተረድተው እንደሆነ የሚገመግሙበት ወቅት ላይ ደርሰዋል። እያንዳንዱ ርእስ ቀርቦ ክፍለ ትምህርቱ እስከሚያልቅበት ድረስ ተከታታይ ምዘና በማድረግ ጭምር ተማሪዎችም የተላለፉትን ጽንሰ ሐሳቦች መቅሰማቸውን ይፈትሹ። ተማሪዎች አጥጋቢ ብቃት ላይ ናቸው ለማለት የሚያስችልዎት፡-

1. የአፈርን ምንነት የገለፁ እንደሆነ፣ አይነታቸውን የለዩ እንደሆነና ጥቅማቸውን መዘርዘር የቻሉ እንደሆነ ነው። የአፈር አጠባበቅ ዘዴዎችንም ማብራራት የቻሉ እንደሆነ ነው።
2. የውሃን ምንነት ለይተው መገኛውን መጠቆም ሲችሉ ነው። ውሃ እንዴት እንደሚበከልና ከብክለት ለመጠበቅ የሚያስችሉ አንዳንድ ዘዴዎችን የተናገሩና ያሳዩ እንደሆነ ነው።

በተጨማሪም ውሃን በቁጠባ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ማስረዳት የቻሉ እንደሆነ

ነው።

3. የአየርን ትርጉም፣ጥቅምና የአየር ብክለትን የመከላከያ ዘዴዎች መግለፅ የቻሉ እንደሆነ ነው።
4. ደን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሲያስረዱ ነው። የደንን ጥቅምና ለደን መደረግ የሚገባውን እንክብካቤ ማስረዳት ሲችሉ ነው።
5. የዱር እንሰሳት ምን እንደሆኑ፣የሚሰጡት አገልግሎት ምን እንደሆነ መዘርዘር ሲችሉና ለዱር እንሰሳቱ የሚደረገው ጥበቃ ምን ምን እንደሆነ ማስረዳት ሲችሉ ነው።

ከአጥጋቢ ብቃት በላይ የሚያስመዘግቡ ተማሪዎችን ማበረታታት፣መሸለም ያስፈልጋል።

እንዲሁም ከአጥጋቢ ብቃት በታች የሆኑ ተማሪዎችን ለይቶ ተጨማሪ ክትትል ማድረግና ተጨማሪ ጊዜ ወስደው የማብቃት ሥራ መስራት ይጠበቅብዎታል።

## የመልመጃ 2.1 መልሶች

ሀ. 1. እውነት 5. እውነት

2. ሃሰት 6. ሃሰት

3. እውነት 7. እውነት

4. ሃሰት

ለ. 1. ሐ 4. መ

2. ሀ 5. ሠ

3. ለ.

ሐ. 1. ለ

4. መ

2. መ 5. ለ

3. መ 6. ሀ

መ. 1. መልሱ የተለያየ ሊሆን ይችላል። በሁሉም አካባቢ ሰዎች ከሞላጎደል ውሃን

- ለመጠጥ፣ለመታጠብያ፣ለእንስሳት
- ለግብርና ሥራ
- ለፋብሪካዎች ወዘተ ሊጠቀሙ ይችላሉ

2. ደን እንዳይመናመን በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች ያለውን ደን መንከባከብ

- አንድ ዛፍ እንኳ ቢቆረጥ ወዲያው መተካት
- ችግኞችን መትከል
- ከእሳት መጠበቅ
- ያለ አግባብ ደንን አለመጠቀም ወዘተ..

በቀበሌና በመንግሥት ደረጃ፡-

- ህዝቡን ስለደን ጥቅምና አጠባበቅ ማስተማር
- ደንን መጠበቅ የሚያስችል ህግ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ የመሳሰሉትን መልሶች ሊሰጡ ይችላሉ

3. መልሱ እንደየአካባቢው ሊለያዩ ይችላል

ለምሳሌ ጅብ፣ጦጣ፣ጉሬዛና ዝንጀሮ ሊጠቀሱ ይችላሉ

ሠንጠረዥ **2.1** የዱር እንስሳት ባህርይ በከፊል

| ተ.ቁ | የዱር እንሰሳው ስም | አመጋገብ | እንቅስቃሴው | አኗኗሩ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጅብ | ሥጋ በል ነው | ይራመዳል | በጫካና ጉድጓድ |
| 2 | ጦጣ | በአብዛኛው ፍራፍሬና ጥራጥሬ | ትራመዳለች (ከዛፍ ዛፍ በመንጠልጠል) | በጫካ ውስጥ በዛፍ ላይ |
| 3 | ጉሬዛ | በአብዛኛው ፍራፍሬና ጥራጥሬ | ይራመዳል (ከዛፍ ዛፍ በመንጠልጠል) | በጫካ ውስጥ በዛፍ ላይ |

4. አየርን የሚበክሉ ነገሮች

- የፋብሪካዎች ጭስ
- የመኪና ጭስ
- በአካባቢው የሚቃጠሉ ነገሮች እንደጐማ ፣ቆሻሻ፣ለከሰልና ለእርሻ ሲባል የሚቃጠሉ ዛፎች ወዘተ
- ፀረ-አረም እና ፀረ -ተባይ መድሐኒቶች
- ከፋብሪካ የሚወጡ ቆሻሻ ኬሚካሎች

መፍትሄ - ለእርሻም ሆነ ለከሰል ደኖችን መንጥሮ አለማቃጠል

- ፀረ- አረም እና ፀረ-ተባይ መድሀኒቶች አየርን እንዳይበክሉ ማድረግ ለምሳሌ የተሻሉ አየርን የማይበክሉ ዘዴዎችን መጠቀም
- የፋብሪካ ጭስን መቀነስ
- የመኪና ጭስን መቀነስ

- ጭስ አልባ የኃይል ምንጭ ለመጠቀም መሞከር
- መንግስት ከባለ ኢንዱስትሪዎች ጋር ስለ አየር ብክለት ውይይት ማድረግና የጋራ መፍትሔ ማምጣትና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

## 2.2. ኃይል

የተመደበለት ጊዜ **18** ክ/ጊዜ

### 1. ዝርዝር ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ፡-

- ሙቀት የኃይል ዓይነት እንደሆነ ይገልፃሉ።
- የሙቀትን ውጤት ቀላል ተግባራዊ ክንዋኔ በማድረግ ያሳያሉ።
- ብርሃን የኃይል ዓይነት መሆኑን ወረቀትና የእጅ ሌንስ ወይም አጉልቶ የሚያሳይ መነፅር በመጠቀም በማቃጠል ያሳያሉ።

### 2. ዝርዘር ይዘቶች

- ሙቀት
- ብርሃን

### 3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

መምህር! በአካባቢያቸው ሰዎች ምግብ ለማብሰል፣ቤታቸውን ለማሞቅና ልብሶቻቸውን አጥበው ለማድረቅ ምን እንደሚጠቀሙ ተማሪዎችዎን በመጠየቅ ይጀምሩ። በመቀጠልም የኃይልን ምንነት ይግለፁላቸው።

ኃይል በተለያዩ መልኮች /ዓይነቶች/ ማለትም በሙቀት፣ በብርሃን፣በኤሌክትሪክ እና በድምፅ መልክ ይገኛል ብለው ያስረዷቸው።

ኃይል ሥራን መሥራት የሚያስችል አቅም ማለት መሆኑን ይግለፁላቸው። ኃይል ከተለያዩ ምንጮች እንደሚገኝም ተማሪዎችን በመጠያየቅ ያስረዱ። የሙቀት ኃይል ውጤቶችን ለማሳየት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተዘረዘሩትን ተግባራዊ ክንዋኔዎች በክፍል ውስጥ እንዲያከናውኑ ይርዷቸው።

በመጀመሪያ ተግባራዊ ክንዋኔ 2.1 ሙቀት ነገሮችን እንደሚያሞቅ የሚያሳየውን ያሰሯቸው። በዚህ ተግባራዊ ክንዋኔ ሙቀት ነገሮችን እንዲሞቁ የሚያደርገው በንክኪ መሆኑን ተማሪዎች እንዲገነዘቡ ሊያስምሩበት ይገባል። ተማሪዎች ተግባራዊ ክንዋኔውን ሲሰሩ ድርጊቶችንና ውጤቶችን እየመዘገቡ እንዲገልፁ ልምድ ማሳደር ይጠበቅብዎታል።

ተግባራዊ ክንዋኔ 2.2 ሙቀት የነገሮችን ቅርፅና መጠን መለወጥ መቻሉን የሚያሳየውን ቀጥለው ያሰሯቸው። በዚህ ተግባራዊ ክንዋኔ ሙቀት ጀላቲ ወይም በረዶ፣ጠጣር ነገር ወደ ፈሳሽነት /ውሃ/፣ፈሳሹን

ደግሞ ወደ እንፋሎት /ጋስ/ መለወጡንና ውሃ በጠጣር፣በፈሳሽና በእንፋሎት መልክ ሊገኝ መቻሉን ያረጋግጡላቸው።

ብርሃን የሃይል ዓይነት መሆኑን በመግለፅ ከልዩ ልዩ ተፈጥሮአዊና ሠው ሰራሽ ምንጮች እንደሚገኝ ያስረዷቸው። ፀሀይ ዋነኛዋ የብርሃን ኃይል ምንጭ መሆኗን ይግለጹ።

ብርሃን የሀይል ዓይነት በመሆኑ ከፀሐይ የሚገኘውን የብርሃን ኃይል ተጠቅመን በሌንስ በመሰብሰብ ወደ ሙቀት ኃይል መቀየር /እሳት መፍጠር/እንደሚቻልና ወረቀቶችንና የእንስሳትን ደረቅ ፍግ ማቃጠል መቻሉን ከተግባራዊ ክንዋኔ 2.3 መረዳት እንደሚችሉ ያስገንዝቡ።

ተግባራዊ ክንዋኔ 2.3 ን በሚገባ መሥራት እንዲችሉና ከውጤት ላይ እንዲደርሱ ይርዷቸው።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የብረት ቁራጭ
- ገል
- የመስታወት ስባሪ
- በረዶ ወይም ጀላቲ
- ብረት ድስት፣ቡታጋዝ ወይም የሚነድ እሳት
- ሙቀት ሌሎችን ነገሮች ሲያሞቅ የሚያሳይ ሥዕል
- ሙቀት የነገሮችን ቅርፅ ሲለውጥ የሚያሳይ ሥዕል
- የፀሐይ ብርሃን ኃይል እሳት /ሙቀት/ሲፈጥር የሚያሳይ ሥዕል

## 5. የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎች

መምህር ክፍለ ትምህርቱ እስከሚያልቅበት ድረስ ተከታታይ ምዘና በማድረግ በተገለፁት ጽንሰ ሐሳቦች ላይ በመመሥረት ተማሪዎች የሚገኙበትን ደረጃ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ተማሪዎች አጥጋቢ ብቃት ላይ ናቸው ለማለት የሚቻለው፡-

1. ሙቀት፣ብርሃንና ድምጽ የኃይል ዓይነቶች እንደሆኑ በተግባራዊ ክንዋኔ የመረዳት ችሎታ ሲኖራቸው
2. የፀሐይ ብርሃን ኃይል በነገሮች ላይ ሲያርፍ ወደ ሙቀት ኃይል እንደሚለወጥ ሲገነዘቡ ነው።

ከአጥጋቢ ብቃት በላይ የሚገኙ ተማሪዎች ለወደፊቱም ችሎታቸውን የበለጠ እንዲያዳብሩ ማበረታታት፣መሸለም ይጠበቅብዎታል። ከአጥጋቢ ውጤት በታች የሚገኙ ተማሪዎች ክትትል ተደርጎላቸው ተጨማሪ ጊዜ ወስደው የማብቃት ሥራ ሊሰሩ ይገባዎታል።

**የመልመጃ 2.2 መልሶች**

ሀ. 1. ሀሰት

2. እውነት

3. እውነት

ለ. 1. አይቻልም። ምክንያቱም የተፈጥሮ የብርሃን ሀይል ስላልሆኑ ነው።

2. ፀሐይ፣ኤሌክትሪክ፣ሻማ፣ኩራዝ የመሳሰሉት ናቸው

ሐ. 1. መልሱ የተለያየ ሊሆን ይችላል

2.. ሙቀት ለመስጠት ነው።

# 2.3 ጉልበት

የተመደበለት ጊዜ **20** ክ/ጊዜ

**1.** ዝርዝር ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ጉልበት በአንድ አካል ላይ ሲተገበር የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ይለያዩ።
- ቀላል መሣሪያዎችን ይለያሉ፣ጥቅማቸውን ይዘረዝራሉ፣ መሣሪያዎቹንም አዘጋጅተው መጠቀም ይችላሉ፣
- ድምፅ የሚፈጠረው በነገሮች መርገብገብ መሆኑን ይገልፃሉ፣ በጠጣር በፈሳሽና በአየር ውስጥ መተላለፉን ያረጋግጣሉ።
- የሙዚቃ መሣሪዎችን ባህላዊ እና ዘመናዊ በማለት በሁለት ይመድባሉ። ለእያንዳንዳቸውም ምድብ ምሳሌ ይሰጣሉ።

**2.** ዝረዝር ይዘቶች

- ጉልበት
- ቀላል መሣሪያዎች
- ድምፅ

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

ስለጉልበት ሲያስተምሩ በተግባራዊ ክንዋኔ ተደግፈው ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም በዚህ ክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች ድርጊቱን እያከናወኑና ውጤቱን እያዩ ቢማሩ ይበልጥ ፍሬአማ ስለሚሆኑ ነው። በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ እንደቀረበው ተማሪዎቹ የተለያዩ ድርጊቶችን እየፈፀሙ የድርጊቱ መግለጫ አብሮት ቢሰጥ ለተማሪዎቹም ለእርስዎም የሚመች ይሆናል።

ጉልበት አራት መሠረታዊ ነገሮችን ያከናውናል፡-

1. አንድን የቆመ አካል ወደ እንቅስቃሴ ውስጥ ያስገባል።
2. በእንቅቃሴ ላይ ያለን አካል እንዲቆም ያደርጋል።
3. በእንቅስቃሴ ላይ ያለን አካል አቅጣጫውን እንዲቀይር ያደርጋል።

4. የአንድን አካል ቅርፅ ይለውጣል። ከዚህ በላይ የተገለፁትን ጽንሰ ሀሳቦች ተማሪዎቹ በእርስዎ እየታገዙ ራሳቸው ተግባራዊ ክንዋኔ እንዲያካሂዱ ይርዷቸው።

የሚያስፈልጉ ነገሮች፡-

- መዶሻ፣
- አገልግሎቱን የጨረሰ ማሰሮና ኳስ ናቸው።

ወንድና ሴት ተማሪዎች ተግባራዊ ክንዋኔውን እንዲያሳዩ ይጋብዙ። አሠራሩ ሴቷ ልጅ በወለሉ ላይ የተቀመጠችውን ኳስ በትንሹ ታንቀሳቅስ።

- ልጂቱ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ኳሷን ስታንቀሳቅስ ልጁ እየተንቀሳቀሰች ያለችውን ኳስ ያቁማት።
- ለሦስተኛ ጊዜ ሴቷ ልጅ ኳሷን ስታቀሳቅስ ወንዱ ልጅ ኳሷን ነካ አድርጎ አቅጣጫዋን ያስለወጥ።
- በአራተኛ ደረጃ ማሰሮውን በመዶሻ መሰባበር ነው። አራቱም ተግባራዊ ክንዋኔዎች የጉልበትን አገልግሎት ያሳያሉ ይበሏቸው። በፋብሪካ፣በእርሻ ላይ፣በቤት ውስጥ፣በጨዋታ ጊዜ ወዘተ ጉልበትን እንደሚጠቀሙ ያስገንዝቧቸው። የጉልበትን ትርጉም ተረድተው ሌሎች የጉልበት ጥቅሞችን በሰፊው እንዲወያዩባቸው ይገፋፏቸው።
- ጉልበት ሥራን ለመሥራት ያስችላል። ሆኖም አንድ ግድግዳ ሲገፋ የቆየ ልጅ ሥራ ሠርቷል ለማለት ይቻላል?
- ሥራ ተሰራ የሚባለው ጉልበት ያረፈበት አካል ሲንቀሳቀስ ብቻ ነው። ብለው ይደምድሙላቸው።
- ቀላል መሣሪያች የጉልበትን አጠቃቀም የሚያዳብሩ ጠቃሚ መሣሪያዎች መሆናቸውን ይግለፁላቸው።
- ቀላል መሣሪያዎች በትንሽ ጉልበት ብዙ አድካሚ ሊሆኑ የሚችሉትን ሥራዎች መሥራት ያስችላሉ በማለት እንደ መዶሻ መቀስ፣የለስላሳ መክፈቻ ወዘተ የመሣሠሉትን ይጥቀሱላቸው።
- በስላች ወለል ያጋደለ ወለል፣ በመፈንቅልና በመዘውር ወይም በከራ ላይ ትምህርት ለመስጠት ተማሪዎችንና የአካባቢ ሰዎችን በማስተባበር ሙሉ በሙሉ ተግባር ላይ ያተኮረ ትምህርት መስጠት ይጠበቅብዎታል። ተማሪዎቹን ከቀላል የአካባቢ

ቁሳቁሶች ሰርተው መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ እንደ ተጠቀሰው እንዲጠቀሙባቸውና አገልግሎታቸውንም በግልፅ መረዳት እንዲችሉ ይርዷቸው።

ድምፅ በነገሮች መርገብገብ እንደሚፈጠርና ለመስማት የድምፅ ምንጭ፣የድምፅ አስተላላፊ እና የድምፅ ተቀባይ እንደሚያስፈልጉ በምሣሌ ይግለፁላቸው። ከሶስቱ አንዱ ቢጐድል እንኳ ድምፅ መስማት እንደማይቻል ተማሪዎቹ እንዲገነዘቡ ያድርጓቸው።

ድምፅ በምን በምን እንደሚተላለፍ በማወያየት ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲያንሸራሽሩ ከአደረጉ በኋላ ድምፅ በጠጣር ነገሮች፣ በፈሳሽና በአየር አማካይነት እንደሚተላለፍ ያብራሩላቸው።

ድምፅ በጠጣር ነገር፣በፈሳሽና በአየር እንዴት እንደሚተላለፍ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተዘረዘሩትን ተግባራዊ ክንዋኔዎች በማሠራት ተማሪዎቹ ራሳቸው ወደ ማጠቃለያ/ድምዳሜ/ እንዲደርሱ ያግዟቸው። በመጨረሻም ድምፅ የኃይል ዓይነት መሆኑን በመንገር ያጠቃሉ።

የሙዚቃ መሣሪያዎች ድምፅ የሚፈጥሩት በገመዶችና በውስጣቸው ባለው አየር መርገብገብ እንደሆነ ተማሪዎች እንዲያስተውሉ ያድርጉ። የምት የሙዚቃ መሣሪያ እንደ ከበሮና ድቤ ያሉት ድምፅ የሚፈጥሩት የተሸፈኑበት ቆዳ ሲርገበገብ መሆኑን እንዲያጤኑ ያደርጋል።

የሙዚቃ መሣሪያዎች ባህላዊና ዘመናዊ በመባል በሁለት እንደሚከፈሉና በሁለቱም የሙዚቃ መሣሪያዎች የገመድ የትንፋሽና የምት መሣሪያዎች እንዳሉ በመማሪያው መጽሐፉ ውስጥ በሰንጠረዡ ተካትቶ ቀርቧል። ሠንጠረዡን በመጠቀም የተጠቀሱትን ምሳሌዎች በመጥቀስ ያብራሩላቸው። ተማሪዎች በአካባቢያቸው ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን መሣሪያዎች የገመድ የትንፋሽና የምት ብለው እንዲለዩ ያድርጉ። በአከባቢያቸው ከሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶች የሙዚቃ መሣሪያዎች እንዲሰሩ ያድርጉ። የሙዚቃ መሣሪያ መጫወት የሚችሉ ካሉም ለክፍል ተማሪዎች ተጫውተው እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው።

## 4.የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የብረት ቁራጭ/ቀጭን / ገል እና የመስታወት ስባሪ
- ኩራዝ/ሻማ/ ኩብሪት
- መቆንጠንጫ ወይም ማስደገፊያ እንጨት
- በረዶ /ጀላቲ/ ብረት ድስት
- ቡታ ጋዝ ወይም የሚነድ እሳት /የኃይል ምንጭ/
- የሙቀት ኃይል ሌሎች ነገሮችን ሲያሞቅ የሚያሳይ ሥዕል
- የሙቀት ኃይል ነገሮችን /የበረዶ፣የቅቤና ሞራን/ቅርፅ ሲለውጥ የሚያሳይ ስዕል

- ከፀሐይ ብርሃን የሚገኘው ሃይል እሳት ሲፈጥር የሚያሳይ ሥዕል
- ድምፅ በጠጣር ነገር አማካይነት ሲተላለፍ የሚያሳይ ሥዕል
- ድምፅ በፈሳሽ ነገር አማካይነት ሲተላለፍ የሚያሳይ ሥዕል
- ልዩ ልዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን የሚያሳይ ሥዕል
- ልዩ ልዩ ዘመናዊ መሣሪያዎችን ሚያሳይ ሥዕል

## 5. የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎች

ተማሪዎቹ እንዲሠሩት የቀረበውን ተግባራዊ ክንዋኔ በተቀመጠለት መንገድ አከናውነው ሙቀት ነገሮችን እንደሚያሞቅ ማረጋገጥ መቻላቸውን ተከታትለው ይዩ/ይገምግሙ።

- ሙቀት በረዶውን ማቅለጡንና ወደ ፈሳሽነት መለወጡን፣ ፈሳሹን ደግሞ ወደ እንፋሎት መለወጡን ተማሪዎች ሰርተው ማየታቸውን ይገምግሙ።
- የፀሐይ በርሃን ኃይል ከፀሐይ ጨረር በሌንስ ሰብስበው ወረቀት ማቃጠል መቻላቸውንና ብርሃን የኃይል ዓይነት መሆኑን ማጠቃለያ ላይ መድረሳቸውን ይገምግሙ
- መምህር ክፍለ ትምህርቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በየደረጃው ተከታታይ ምዘና በማድረግ በተገለፁ ጽንሰ ሀሳቦች ላይ በመመሥረት ተማሪዎች የሚገኙበትን ደረጃ ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል።

ተማሪዎች አጥጋቢ ብቃት ላይ ናቸው የሚባሉት፡-

- ሙቀት፣ ብርሃንና ድምፅ የኃይል ዓይነት መሆናቸውን ሲረዱና በሙከራ/ተግባራዊ ክንዋኔ/ሲያረጋግጡ ነው።
- ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለይተው ምሳሌዎችን መስጠት ሲችሉ፣
- የጉልበት ትርጉምና ውጤቱን ማሳየት ሲችሉና
- የቀላል መሣሪያዎች ጥቅምና ምሳሌ በመስጠት በተግባር ማሳየት ችለው ሲገኙ ነው።
- ከአጥጋቢ ብቃት በላይ የሚገኙትን ተማሪዎች ማበረታታት ለወደፊቱ ውጤታቸው እንዲሻሻል ይረዳቸዋል። እንደዚሁም ከአጥጋቢ ውጤት በታች ወርደው የሚገኙት ተማሪዎች ተለይተው ተጨማሪ ጊዜ በመውሰድ የማብቃት ሥራ መስራት ይጠበቅብዎታል።

## የመልመጃ 2.3 መልሶች

ሀ. 1. እውነት

2. ሃሰት

3. እውነት

4. አውነት

ለ. 1. መ

2. ሀ

3. ለ

ሐ 1. ሀ 4. መ

2. ለ 5. መ

3. መ

## የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

ሀ.

1. ሀሰት

2. እውነት

3. እውነት

4. እውነት

ሐ.

1. ለ

2. መ

3. መ

4. ሠ

5. ሀሰት 5. ለ

ለ. 1. ሠ

2. ሐ

3. ሀ

4. ለ

5. መ

መ. 1. ለቤት መሥሪያ፣ለእርሻ ቦታ ፍለጋ ፣ለማገዶ/ከሰል/ወዘተ የመማሪያ መጽሐፉን

ይመልከቱ

የዱር እንስሳት ጥቅሞች በመማሪያ መጽሐፉ ተጠቅሰዋል ለእንስሳቱ ሊደረግ የሚገባው ጥበቃም በመማሪያ መጽሐፉ ተካቷል። /3.4/ የመማሪያ መጽሐፉን ይመልከቱ።

# ክፍለ ትምህርት ሶስት

# በማህበረሰባችን ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት

የተመደበው ጊዜ **42** ክፍለ ጊዜ

*መግቢያ*

በዚህ ክፍለ ትምህርት የሚተኮርባቸው ዋና ዋና የትምህርት ርዕሶች ሁለት ናቸው። እነሱም አርሻና በአካባቢው የኢንዱስትሪ ምርቶች የሚሉ ሲሆኑ በነዚህም ርዕሶች ስር ዝርዝር ነጥቦች ማለትም ለእፅዋትና ለሰብል እድገት የአፈር ጠቀሜታ፣ እፅዋትን መትከልና መንከባከብ፣ ጎጂ ነፍሳት በሰው ላይ የሚያስከተሉት ችግር፣ ንብ የማርባት ጥቅም፣ ትንንሽ እንስሳትን ማጥናት፣ በአካባቢያችን የሚመረቱ ምርቶችና ገዥና ሻጭ ያላቸው ግንኙነት የሚሉት ቀርበዋል። በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የተማሪዎቹ የመማር ብቃታቸውን ለማሳደግ የትምህርቱ አቀራረብ አሳታፊና ሳቢ እንዲሆን ማመቻቸት ይገባል።

**አጠቃላይ ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- አፈር ለእህል ምርት አስፈላጊ መሆኑን፣የመደብ ዝግጅት፣ ለእፅዋትና ለእህል ምርት መደረግ የሚገባውን እንክብካቤ ይገልፃሉ።
- የእህል ምርትና እፀዋትን የሚያጠቁና የሚያበላሹ እንስሳትን ይለያሉ፣ የሚደርሰውንም ጥፋት እንዴት መከላከል እንደሚቻል ይገልፃሉ።
- የንብ አናቢነትን ጥቅምና የንብን የመራባት ሁኔታ ያስረዳሉ።
- በነፍሳት ላይ ቀላል የሆነ የተግባር ሙከራ ያሳያሉ።
- በአካባቢያቸው የሚመረቱ ምርቶችን ይለያሉ፣ተፈላጊነታቸውንም ይገልፃሉ።
- በሻጭና ገዥ መካከል ያለውን የተቀናጀ ግንኙነት ይገልፃሉ።

## **3.1** እርሻ

የተመደበው ጊዜ **30** ክፍለ ጊዜ

1. ዝርዝር ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-
   - አፈር ለእህል ምርት ያለውን ጠቃሚነት ይናገራሉ።
   - የዋልካ አፈር ለእፀዋት እድገት እጅግ ተፈላጊ መሆኑን ይለያሉ።
   - ዘር ለመዝራት የሚያስችል መደብ ያዘጋጃሉ
   - ማደግ ላይ የሚገኙ እፀዋትን ይንከባከባሉ።
   - አንበጣ፣ አይጥና አእዋፍ በምርት ላይ ሊያደርሱት የሚችሉትን ጉዳት ይገልፃሉ።
   - የንብ እናቢን ጥቅም ያስረዳሉ።
   - የዝንብን፣ የወባ ትንኝን፣ የንብንና የአንበጣን ውጫዊ ክፍል አጉሊ መነፅር በመጠቀም

     ያጠናሉ። ይህንንም ይገልፃሉ።

**2.** ዝርዝር ይዘቶች

- አፈርና የእህል ምርት
- የአፈር ጥቅም
- ለእፅዋት እድገት የበለጠ ጥሩ አፈር(ዋልካ አፈር)
- እፅዋትን መትከልና መንከባከብ
- ጎጂ ነፍሳት
  - የመዋለድ ዑደት
  - ጉዳትና ጉዳትን መከላከል።
- ንብ እናቢ
  - ጠቀሜታ
  - የንብ ዑደተ- ሕይወት
- ትንንሽ እንስሳትን ማጥናት

መግለጫ

አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚኖረው በገጠር ሲሆን የሚተዳደረውም በግብርና ሙያ ነው። ከግብርና ሙያ ውስጥ ዋነኛው የእርሻ ሥራ ነው። እርሻ ልዩ ልዩ የምግብ ሰብሎች፣ የቅባት እህሎችና አትክልትና ፍራፍሬዎች የሚመረቱበት የሥራ ዘርፍ ነው።

አፈር ለእፅዋት እድገት አስፈላጊ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ነው።

እፀዋት - ቀጥ ብለው እንዲቆሙና እንዲያድጉ፣

- ለእድገታቸው አስፈላጊ የሆኑ ውሃና የማእድናት ንጥረ ነገሮች እንዲያገኙ ይረዳል።

አፈር አሸዋማ፣ ሸክላና ዋልካ (ድብልቅ) በመባል የሚታወቁ የአፈር ዓይነቶች አሉት። ከነዚህም ውስጥ ለእፀዋት እድገት በጣም ተስማሚ፣ ለምና ምርታማ አፈር የሚባለው ድብልቅ (ዋልካ) የተሰኘው ነው።

የእፀዋትን ዘር ለመዝራት ወይም ችግኝ ለመትከልና ለመንከባከብ እንዲቻል የመደብ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። ተቆፍሮና ለስልሶ በተዘጋጀው መደብ ላይ በመስመር ወይም በብተና ዘዴ መዝራት ይቻላል። የተተከሉትን እፅዋት ለመንከባከብ ውሃ ማጠጣት፣አረሞችን መንቀል፣ ማዳበሪያ መጨመር፣ ተክሎችን ከሚያጠቁ ተባዮች መከላከልና መኮትኮት ተገቢ ነው። በተገቢው እንክብካቤና ክትትል ያደጉትን እፅዋት(ሰብሎች) ለመሰብሰብ ሲደርሱ በትክክለኛው ጊዜ መሰብሰብና ጥቅም ላይ ማዋል ጥሩ ነው። ሰብሎቹ የሚከማቹባቸው ጎተራዎችና መጋዘኖችን ማፅዳትና የፀረ እህል ተባይ መድኃኒቶችን መርጨት ያስፈልጋል።

ነፍሳት በአካል አወቃቀራቸው የሚመሳሰሉና ራስ፣ደረትና ሰውነት በመባል የሚጠሩ ሶስት ዋና ዋና የአካል ክፍሎች አሏቸው። እንደዝንብና የወባ ትንኝ ያሉ በሰው ልጅ ህይወት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ጎጂ ነፍሳት ናቸው። አራት የእድገት ደረጃዎችም ማለትም እቁላልን፣ እጭን፣ሙሽሬን(ፑፓን) እና ጉልምስን (ሙሉ የነፍሳት ሰውነት) ያካተተ የህይወት ወይም የመዋለድ ዑደት አላቸው።

ዝንብ በቆሻሻ ቦታዎች፣ የወባ ትንኝ ደግሞ በየአካባቢው በረጋና በተቋጠረ ውሃ ውስጥ በመራባት በሰው ላይ በሽታዎችን የሚያስከትሉ ጀርሞችን በማስተላለፍ የሚታወቁ ጎጂ ነፍሳት ናቸው።

በዝንቦች አማካይነት በሚተላለፉ ጀርሞች የሚመጡ በሽታዎች ኮሌራ፣ ታይፎይድ፣ ትራኮማና አሜባ የመሳሰሉት ናቸው። የወባ ትንኝ ደግሞ የወባ በሽታ የሚያስከትሉትን ጀርሞች ታስተላልፋለች።

ንቦች ማር በመስራት የሚታወቁ ጠቃሚ ነፍሳት ናቸው። ንቦችን በባህላዊና በዘመናዊ ቀፎዎች ማርባት የሚቻል ሲሆን አበባዎችን በመቅሰም ማር፣ሰምና የማር ሙጫን ያበረክታሉ። ንቦች በጋራ የመኖር ተፈጥሮአዊ ልምድ ያላቸውና ማህበራዊ ነፍሳት (social insects) በመባል የሚታወቁ ናቸው። በአንድ የንብ ቀፎ ውስጥም ንግስት፣ ድንጉልና ሠራተኛ ንቦችን በማካተት በብዙ ሺህ የመቆጠሩ ንቦች በጋራ ይኖራሉ።

ትንንሽ እንስሳት ማለትም እንደ ዝንብ፣ የወባ ትንኝ፣ እንበጣና ንብ የመሳሰሉ ነፍሳት ሶስት ተመሳሳይ የአካል ክፍሎች አሏቸው። ዝንቦች፣ የወባ ትንኞችና ንቦች ፈሳሽ ምግቦችን በመምጠጥ ለመመገብ የሚያስችል ፕሮቦሲስ የሚባል ቀጭን ቱቦ የአፍ አካል፣ ሁለት ክንፎችና ስድስት እግሮች አሏቸው።

አንበጣዎች ደግሞ መንጋ በመፍጠርና ከቦታ ቦታ በጋራ በመብረር ሰብሎችን በመብላትና በማውደም በከፍተኛ ፍጥነት ጉዳት ያደርሳሉ። ቅጠልን መንከስና መቁረጥ የሚችል የመንከሻ አፍ፣ አራት ክንፎችና ስድስት እግሮች አሏቸው።

3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

- በተለያዩ አካባቢዎች ሚኖሩ ሰዎች ኑሮ የተመሰረተው እንደየአካባቢው ሁኔታ በተለያዩ ስራዎች ነው። ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው የሚኖሩ ሰዎች ኑሮአቸው የተመሰረተው ምን ምን ስራዎችን በመስራት እንደሆነ ዘርዝረው እንዲናገሩ በትምርህቱ መግቢያ ለማነቃቂያ ይጠይቋቸው። የሚሰጡት መልስ የተለያየ ሊሆን ይችላል። እያበረታቱ ይቀበሏቸውና በከተማና በገጠር የሚኖሩ ሰዎች የተለያዩ ስራዎች እንደሚሰሩ

ለምሳሌ፡- በከተማ ያሉ ሰዎች በንግድ ስራ፣ በቢሮ ስራ በህክምና ስራና በሌሎችም ስራዎች

እንደሚሰማሩ፣ አብዛኛው የገጠር ሰው ደግሞ የሚተዳደረው በግብርና ሙያ እንደሆነና በእርሻ ስራ እንዲሁም በእንስሳት እርባታ መሆኑን ያብራሩላቸው።

- እርሻ ትልቁ የግብርና ሙያ ዘርፍ እንደሆነና አብዛኛው የገጠር ሰዎች የኑሮ መሰረት መሆኑን ይንገሯቸው። በእርሻ ስራ ምን ምን እንደሚመረቱ እንዲናገሩ ለተማሪዎቹ የክፍል ስራ ይስጧቸው። ከዚያም በእርሻ ስራ ልዩ ልዩ የምግብ ሰብሎችን፣ የቅባት እህሎችን፣ አትክልትና ፍራፍሬዎችን የሚመረቱበት የግብርና ዘርፍ እንደሆነ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተገለጹትን በመዘርዘር እንዲረዱ ያድርጉ፡
- አፈርና የእህል ምርት የሚለው ርዕስ ከመግባትዎ በፊት ተማሪዎቹ ስለአፈር ጥቅም የሚያውቁትን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። በሚያቀርቧቸውም መልሶች ተንተርሰው፡-
- አፈር ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑ የምግብ ሰብሎች የሚመረቱበት የተፈጥሮ ሀብት መሆኑን፣
    - በመሬት ላይ ለሚበቅሉ እፅዋት ሁሉ የእድገት መሰረት እንደሆነ
    - ውሃና አስፈላጊ ንጥረ ምግቦችን ከዚያው ከአፈር ውስጥ እንዲያገኙ እንደሚረዳቸው ያስረዷቸው።
- አፈር ከልዩ ልዩ ትንንሽ የአፈር ቅንጣቶች የተሰራ መሆኑን ሶስቱን የአፈር ዓይነቶች በመዘርዘር ይግለጹላቸው። ይኸውም፡-
- አሸዋማ አፈር የሚሰራባቸው ቅንጣቶች ትልልቅ በመሆናቸው ጠበቅ ያሉ አይደሉም። ውሃ በቀላሉ በውስጡ እንደሚሰርግና ለእፅዋት እድገትም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችም በበቂ ሁኔተ የሌለውና ምቹ እንዳልሆነ እንዲያውቁት ያስረዷቸው።
- የሸክላ አፈር የሚሰራው በጣም ትንንሽ ከሆኑ ቅንጣቶች መሆኑና በጣም ጥበቅ ያለ አፈር ስለሆነ ውሃ ወደ ውስጥ ሰርጎ ከመግባት ይልቅ በላዩ ላይ ተቋጥሮ እንደሚቀመጥ፣ በቂ የውሃና የአየር ዝውውር እንደሌለው፣ በቂ የሆኑ ማእድናትና ብስባሽ የሌለውና ለእፅዋት እድገትም ብዙ ለም አፈር አለመሆኑን ያብራሩላቸው።
- ድብልቅ (ዋልካ) አፈር ደግሞ የአሸዋማና የሸክላ አፈር ድብልቅ መሆኑንና የተሰራባቸውም የአፈር ቅንጣቶች መካከለኛ መጠን ያላቸው መሆኑን
    - በውስጡ በቂ የውሃና አየር ዝውውር እነደሚካሄድ

- በቂ ማእድናትና ብስባሽ ያለው ለምና ምርታማ አፈር በመሆኑ ለእፀዋት እድገት አመቺና በጣም ተፈላጊ መሆኑን ያስረዷቸው።

- በሌላ በኩል ደግሞ አፈር ለም አፈርና ለም ያልሆነ አፈር በመባል በሁለት እንደሚከፈል በማስረዳት የሁለቱንም አፈር ክፍሎች ባህርይ በመማሪያ መጽሐፍ በተገለፁት ዘርዝር ነጥቦች መሰረት ለም(ዋልካ) አፈር ለእፀዋት እድገት የበለጠ ምቹና አስፈላጊ አፈር መሆኑን እንዲሁም ለም ያልሆነው አፈር ለሰብሎች እድገት ተስማሚ አለመሆኑን ያብራሩላቸው። በስዕሉ ላይ የተመለከተው በለምና ለም ባልሆነ አፈር መካከል ያለውን ልዩነት እንዲያስተውሉ ያበረታቷቸው።
- በአንድ አነስተኛ ሳጥን ዋልካ አፈር ወደ ክፍል በማምጣት ተማሪዎቹ እንዲያዩት ያድርጉ እንዲሁም ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው አካባቢ በዋልካ አፈር እፅዋትን በመትከል እድገታችን እንዲከታተሉና ውጤቱን እንዲያስተውሉ ይርዷቸው።
- ተማሪዎቹ የእፀዋት ዘር ለመዝራትና ችግኝ ለማፍላት መደረግ የሚገባቸው ዝግጅቶች ምን ምን እንደሆኑ እንዲወያዩና ሃሳቦችን እንዲያመነጩ ማበረታታት። ከዚያም በተከታታይ የተተከሉ እፀዋትን መንከባከብ ምን መምሰል እንዳለበት በውይይቱ እንዲያነሱ ማድረግ።
- የሰብሎች(የእፀዋት) ዘሮች ለመዝራት መደረግ የሚገባቸው ቅደም ተከተሎች
  - ተስማሚ ስፍራን መምረጥ፣
  - ምንጣሮ ማካሄድ፣
  - ቁፋሮ ማካሄድ፣
  - የችግኝ መደብ ማዘጋጀት፣
  - መደቡን ውሃ ማጠጣትና
  - በመጨረሻም ዘርን መዝራት(ችግኝን መትከል) መሆናቸውን ያብራሩላቸው።
- የእፀዋት ዘርን ለመዝራት በሚዘጋጀው መደብ መካከል ለመተላለፊያ ቀጭን መንገድ መኖር እንዳለበት እንዲሁም ለበጋና ለክረምረት ወቅት የሚዘጋጁ መደቦች እንደሚለያዩ ማስረዳት፣
- ዘር ሲዘራም መደቦቹን ውሃ ማጠጣት እንደሚያስፈልግ ሁለት አይነት የዘር አዘራር ዘዴዎች እንዳሉ፤በመስመር መዝራትና በብተና መዝራት እንደሆኑም ማስረዳት።
- በብተና ከመዝራት ይልቅ በመስመር የመዝራት ዘዴን መጠቀም የበለጠ ጠቅም እንዳለው በመማሪያው መጽሐፍ በተጠቀሰው መሰረት በመግለፅ ያብራሩላቸው።

- ዘር ከተዘራ በኋላ ለመብቀል
  - አየር (ኦክሲጅን)፣
  - ውሃና
  - ተስማሚ ሙቀት

እንደሚያስፈልጉ በመጥቀስ እንዚህም ሁኔታዎች ከተሟሉ ዘሩ ውሃ እንደሚስብና እንደሚወፍር ከሶስት ቀናት በኋላም በቅሎ ወደ ችግኝነት ቀስ በቀስ እንደሚያድግ ማስረዳት በመፅሐፉ ላይ ያሉት ስእሎችን እንዲመለከቱና እንዲያስተውሉ ይርዷቸው።

- የተዘሩ የሰብል ዘሮችን ወይም ችግኞችን በማዛውር የተተከሉ ሰብሎችን እድገት እስከሚሰበሰቡ ጊዜ ድረስ ለመንከባከብ የሚከተሉት ተግባራት መከናወን እንዳለባቸው በመዘርዘር ያስረዷቸው እነዚህም፡-
    1. ውሃ በተገቢው ሰዓት ማጠጣት፣
    2. አረሞችን መንቀል፣
    3. ማዳበሪያ መጨመር፣
    4. ተክሎችን ከተባዮችና ከበሽታ መከላከል፣
    5. መኮትኮት፣
    6. ተክሎች ተደራርበው እንዳይበቅሉ፣ የተደራረቡትንም በመንቀል ማሳሳትና
    7. የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ መሰብሰብ ናቸው።
- በእንክብካቤ ያደጉት ሰብሎች ለምግብነት መድረሳቸውን በማረጋገጥ በወቅቱ መሰብሰብ እንደሚገባ ይህም ሰብሎቹ ጥራታቸው እንዳይቀንስና እንዳይባክኑ እንደሚረዳ ይገለጹላቸው፡
- በወቅቱ ያልተሰበሰቡና ጥቅም ላይ ያልዋሉ ሰብሎች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች ጥራታቸውና መጠናቸው እንዲሚቀንስ ያስረዷቸው።
- ተማሪዎቹ በተከታታይ የተተከሉትን እጽዋት የማንከታተላቸው ከሆነ ሊደርሱ በሚችሉ ችግሮች ላይ እንዲወያዩ የክፍል ስራ ይስጧቸውና የውይይታቸውን ውጤት ከተቀበሉ በኋላ ክትትልና እንክብካቤ ያልተደረገላቸው እጽዋት በተለያዩ ተባዮች እንደሚጠፉና መገኘት የሚገባው የምርት መጠንና ጥራት እንሚቀንስ ያብራሩላቸው።
- በአካባቢያቸው የተተከሉ ሰብሎች ክትትልና እንክብካቤ ሳይደረግላቸው ቀርቶ የደረሰባቸው ችግር ካለ ያዩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲነግሩ ያድርጉ
- የተግባር ክንዋኔውን ማከናወን የተፈለገው ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋል በክፍል ውስጥ የተማሩትን በተግባር ለማሳየት እንዲችሉ ለማድረግ ታስቦ ነው። የአሰራር ቅደም ተከተሉን ጠብቀው የጓሮ አትክልትን በብተናና በመስመር በመዝራትና በመንከባከብ ውጤቱን እንዲያዩ ይከታተሏቸው፡ በመጨረሻም በመስመርና በብተና ዘዴዎች በተዘሩት ሰብሎች መካከል ያለውን ልዩነትና የምርት ውጤት እንዲያወዳድሩ ይርዷቸው።
- ሰብሎች ከመሰብሰባቸው በፊት በማሳ ላይ እንዳሉ የሚደርስባቸውን ጉዳት እንዲዘረዝሩና እንዴት መከላከል እንደሚቻል ሃሳብ እንዲያመነጩ የክፍል ስራ በመስጠት ያሰሯቸው።
- ሰብሎች ከመስበሰባቸው በፊት ገና በማሳ ላይ እንዳሉ በሽታ በሚያስከትሉ ህዋሳትና ተባዮች(እንደ ተምችና አንበጣ) ባሉት እንደሚጠቁ እንዲሁም ግሪሳ የሚባሉ ወፎች ሰብሎቹን በቀጥታ በመመገብና በማራገፍ ጉዳት እንደሚያስከትሉ በማብራራት ያስረዷቸው።
- እነዚህንም ተባዮች ለመከላከል የተባይ ማጥፊያ ኬሚካልን በመርጨት ማጥፋት እንደሚቻል ይጠቁሟቸው።
- የእህል ማከማቻ ጎተራዎችንና መጋዘኖችን ማጽዳትና ተስማሚ ፀረ-ነፍሳት መርዞችን በመርጭት ፀረ-እህል ነፍሳትን መከላከል እንደሚገባ እንዲሁም የምግብ ሰብሎችን

በማጥፋት የታወቁትን አይጦች ለመከላከል አይጦች ይኖራሉ የሚባሉበትን አካባቢዎች መመንጠርና ማጽዳት እንደሚገባ ያስረዷቸው።

- ነፍሳት የሚባሉት ምን ምን አይነት እንደሆኑ ስም ዝርዝር እንዲጠሩ ይጠይቋቸውና ወደ ትምህርቱ ይግቡ። በአጠቃላይ ነፍሳት በአካል አወቃቀራቸው ተመሳሳይነት እንደሚያሳዩ ሶስት የአካል ክፍሎችም እንዳሏቸውና ራስ፣ ደረትና የታችኛው ሰውነት እንደሚባሉም ይግለጹላቸው።
- ከብዙዎች ነፍሳት ውስጥ ጎጂ ነፍሳት የሚባሉትም እንደ ዝንብና የወባ ትንኝ የመሳሰሉት ሲሆኑ በሰዎች ጤንነትና ሕይወት ላይ ጉዳት እንደሚያደርሱ ነግረው እንዚህ ጎጂ ነፍሳት ምን ምን ጉዳት እንደሚያደርሱ እንዲወያዩ የክፍል ስራ ይስጧቸው። የሚያቀርቡትንም መልስ በማሰባሰብ በሽታ አምጪ ጀርሞችን ወደ ጤነኛ ሰው በማስተላለፍ በሽታ ያስከትላሉ ወደ ሚለው ሃሳብ በማዘንበል እንዲረዱ ይርዷቸው
- ዝንቦች ቆሻሻ ባለበት ቦታና በእንስሳት አይነ ምድር እንዲሁም በምግብ ላይ እንቁላል በመጣል እንደሚራቡ ይግለጹላቸው።
- ዝንቦች አራት የሕይወት-ዑደት(የእድገት ደረጃዎች) እንዳሏቸው እንቁላል፣ እጭ፣ ሙሽሬና ጉልምስ በመባል እንደሚታወቁ ያስረዷቸው። በዚህም መሰረት ሴቷ ዝንብ፡- - እንቁላል የምትጥለው በእንስሳት አይነምድርና በምግብ ላይ መሆኑን፣
    - እንቁላሉ በመፈልፈል ወደ እጭነት መቀየሩን፣
    - እጩ ብዙ ቆሻሻዎችን ከተመገበና ከቆየ በኋላ በመሸፈኛ ተሸፍኖ ከእንቅስቃሴና ከመመገብ ውጭ ሆኖ ሙሽሬ(ፑፓ) ወደ ተባለ ደረጃ እንደሚለወጥና
    - በመጨረሻም ሙሉ የዝንብ ሰውነት በመያዝ ጉልምስ ወደ ተባለ ደረጃ በመለወጥ መብረር እንደሚጀምር ያስረዷቸው
- አመቺ ሁኔታ ካለ የዝንቦች የሕይወት ዑደት እንዴት እንደሚከናወን ተማሪዎቹ እንዲያስተዉሉ ለዝንቦች መራባት ምቹ የሆኑ ቆሻሻ ነገሮች ወይም ስጋ በማዘጋጀት በሴቷ ዝንብ የሚጣሉት እንቁላሎች ወደ ነጭና ትል መሰል እጮች መለወጣቸውን እጮቹ ደግሞ ወደ ፑፓ በመጨረሻም ወደ መሉ የዝንብ ሰውነት መለወጣቸውንና አራቱንም የእድገት ደረጃዎች ማከናወናቸውን እንዲያጤኑ ከተማሪዎቹ ጋር አብሮ በመስራት ይርዷቸው።
- ተማሪዎቹ በቆሻሻዎችና በዓይነምድር ላይ የሚገኙ ለጤና ጠንቅ የሆኑ ጀርሞች በዝንቦች አማካይነት ወደ ምግብና ሰውነት እንደሚደርሱ እንዲያውቁ፣ ለተለያዩ በሽታዎችም እንደሚያጋልጡ ከበሽታዎቹም መካከል
    - ኮሌራ፣
    - ታይፎይድ፣
    - ትራኮማና የመሳሰሉት እንደሚገኙባቸው ይግለጹላቸው።
- ጀርሞች ወደ ምግባችንና ሰውነታችን የሚተላለፉት በዝንቦች ብቻ ሳይሆን በትንኞችና በበረሮዎች እንደሚተላለፉ ያስረዷቸው።

- በዝንቦች አማካይነት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል ዝንቦችን ለማጥፋት በሚያስችሉ ዘዴዎች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ

ከዚያም፡- በውሃ አካባቢዎች ባለመጸዳዳት፣

- ንጽህናው በተጠበቀ ሽንት ቤት በመጠቀም፣
- ቆሻሻዎችን ሰብስቦ በማቃጠል፣
- አካባቢን በጋራ በማጽዳት፣
- ውሃን አፍልቶና አቀዝቅዞ በመጠጣት፣
- ምግባችንን በንጽህና በማዘጋጀት፣
- አትክልትና ፍራፍሬን አጥቦ በመመገብ የዝንቦችን መራባትና የበሽታዎችን መሰራጨት መከላከል እንደሚቻል ማብራራት

- የወባ ትንኝን በተመለከተ በሰዎች ላይ ምን ጉዳት እንደምታስከትል ይጠይቋቸውና የሚመልሱትን በማዳመጥ የወባ ትንኝ ለወባ በሽታ መንስኤ የሆኑትን ጀርሞች በበሽታው ከታመመ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው በማስተላለፍ ጉዳት የምታደርስ አደገኛ ነፍሳት መሆኗን ያስረዷቸው።
- የወባ ትንኞች የሚራቡት በረጋ ወይም በተቋጠረ ውሃ ውስጥ ሲሆን እንደ ዝንቦች አራት የእድገት ደረጃዎችም አሏቸው። እንቁላሎችን በረጋ ውሃ ውስጥ ይጥላሉ፣ ወደ እጭነትም ይፈለፈሉና ቆሻሻ እየተመገቡ ይቆያሉ። ከዚያም እጮቹ ምግብ የማይመገቡበትና እንቅስቃሴ ወደ ማያደርጉበት ቱፓ(ሙሽሬ) የእድገት ደረጃ ይለወጣሉ። በመጨረሻም ሙሉ የወባ ትንኝ በመሆን የህይወት ዑደታቸውን እንደሚያጠናቅቁና መብረር እንደሚጀምሩ ያብራሩላቸው
- የወባ ትንኝ የወባ በሽታን የምታስተላልፈው በሽታ አምጪ ህዋሳትን (ጀርሞችን) ተሸክማ ጤነኛ ሰውን በመንከስ (በመንደፍ) ደም በምትመጥበት ጊዜ መሆኑን ተማሪዎቹ እንዲረዱ ማድረግ ያስፈልጋል።
- የወባ በሽታን የምታስተላልፈው ሴት የወባ ትንኝ እንደሆነችና ሴቷ ትንኝ ከታመመ ሰው ደም ስትመጥ የወባ በሽታ ጀርሞችን ከደሙ ጋር አብራ ትመጣለች። ወደጤነኛ ሰውም በመሄድ እንደገና ደም ስትመጥ ጀርሞችን ጤነኛ ሰው ደም ውስጥ ትጨምራለች። ከጥቂት ቀናት በኋላም የወባ በሽተኛ አንደምታደርግ ያብራሩላቸው።
- ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው የወባ በሽታ ተከስቶ እንደሆነና በየትኛው ወር ውስጥ እንደነበር ይጠይቋቸው መልሶቻቸውንም ይቀበሉ። ከዚያም በአገራችን በአብዛኛው የወባ በሽታ የሚከሰቱባቸው ወራት ከመስከረም እስከ ታህሳስ ባሉት ሞቃት ጊዜያት መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ ይገባል።

- የወባ በሽታ አምጪ ጀርሞች ጤነኛ ሰው ደም ውስጥ ከገቡ በኋላ በፍጥነት በመራባት የሰውን ደም ያጠቁና የተለያዩ የወባ በሽታ ምልክቶች ይታያሉ። የወባ በሽታ ምልክቶች ምን ምን እንደሆኑ ተማሪዎቹን ይጠይቋቸው። ከዚያም ምልክቶቹ
  - ትኩሳትና ላብ፣
  - ብርድ ብርድ ማለት፣
  - ማንቀጥቀጥና
  - ማስመለስ መሆናቸውን እንዲረዱ ያድርጓቸው።
- የወባ በሽታ በሰው ልጅ ጤና ላይ የሚያስከትለው ጉዳት በጣም አደገኛ መሆኑን በማስረዳት የህመሙ ምልክቶች እንደታዩ ወዲያውኑ ተገቢውን ህክምና ማግኘትና መዳን እንደሚገባ ህክምና ሳይደረግ ቢዘገይ ወይም ቢቀር ግን በሽታው በቀላሉ ለሞት እንደሚያደርስ ትኩረት በመስጠት ያስረዷቸው።
- ተማሪዎቹ የወባ በሽታ እንዳይነሳ ለመከላከል ምን ምን ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚገባ በቡድን ተወያይተው እንዲመልሱ ይጠይቋቸው። የሚሰጡትንም ሃሳብ ይቀበሏቸው።

  ከዚያም ቀጥሎ በተዘረዘሩት መንገዶች የወባ በሽታን መከላከል እንደሚቻል ያሳውቋቸው።
እነዚህም፡- የወባ ትንኝ መራቢያ የሆኑ ቦታዎችን ማጽዳትና ማድረቅ፣
  - የውሃ ማጠራቀሚያ እቃዎችን መክደን፣
  - የወባ ትንኞች ባሉበት አካባቢ ፀረ-ትንኝ መድሓኒት በመርጨት ማጥፋትና
  - በመኝታ ጊዜ በአልጋ ዙሪያ አጎበር መሸፈን ናቸው።

- የወባ በሽታ እንዳይነሳ ለማድረግና ለመቆጣጠር የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት መሆኑንና ማንኛውም ሰው ቸልተኛ መሆን እንደሌለበትና የግል ተነሳሽነት ሊኖር እንደሚገባ ማስረዳት ተገቢ ይሆናል።

- ንቦችን በተመለከተ ንቦች የሚያስገኙትን ጥቅም እንዲዘረዝሩ ተማሪዎችን ይጠይቋቸው። እነሱም ንቦች ለሰው ልጅ ማርን አምርተው ይሰጣሉ እንደሚሉ ይጠበቃል። መልሳቸውም ልክ ነው። እርስዎም ከእነሱ ሃሳብ በመነሳትና በመደገፍ ንቦች ጠቃሚ ነፍሳት መሆናቸውን፣ አበባ በመቅሰም ማርና ሰምን አምርተው ለሰዎች እንደሚያበረክቱ በማብራራት ትምህርቱን ይጀምሩላቸው።

- የንብ እርባታ ብዙ ቦታና ጊዜ ሳይጠይቅ በቀላሉ የሚከናወን ስራ እንደሆነ፣ በባህላዊ ቀፎና በዘመናዊ ቀፎ ማርባት እንደሚቻል፣ ነገር ግን ሁለቱ ቀፎዎች የሚያስገኙት የማር ብዛትና ጥራት የተለያየ መሆኑን እንዲረዱት ያድርጓቸው።

- ባህላዊ የንብ ቀፎ በአሰራሩ ጠቡብ ያለና አቀማመጡም ለንቦች ኑሮና ስራ አመቺ ባለመሆኑ፡- ንቦችን ለመከታተል እንደማይመች
  - ንቦቹም ለብርድና ለውርጭ እንደሚጋለጡ በዚህም የተነሳ የሚመረተው የማር ብዛትና የጥራት ደረጃው ዝቅተኛ መሆኑን ያስገንዝቧቸው።

- ዘመናዊ የንብ ቀፎ በአሰራሩም ሆነ በአቀማመጡ የተሻለ እንደሆነ፣ ለንቦቹ ማርቢያና ማር ማከማቻ በቂ ቦታ እንዳለው፣ የንቦቹን ሰራ ለመከታተል የሚያመችና የሚመረተውም ማር በጥራትም ሆነ በመጠን ከባህላዊ ቀፎ በጣም የተሻለ እንደሆነ ያስረዷቸው፡
- በአካባቢው ንብ አርቢዎች የሚገኙ ከሆነ ተማሪዎችን በማስጎብኘት ወይም ቀፎዎቹን ወደ ክፍል በማምጣት እንዲመለከቱና ልዩነታቸውን እንዲያተውሉ ይርዷቸው
- ለንቦቹ እርባታ አመቺ ይሆን ዘንድ ቀፎዎቹ በቂ ውሃና አበባ በሚገኝበት አካባቢ አራርቆ በማስቀመጥ የተሻለ የማር ምርት ማግኘት እንደሚቻል እንዲያውቁ ማድረግ ይገባል።
- ንቦች ማር ለመስራት ምን እንደሚያስፈልጋቸው በመጠየቅ ያወያዩአቸው። ከልዩ ልዩ እጽዋትና አበቦች ውስጥ ጣፋጭ ፈሳሽ ቀስመው ማር ይሰራሉ የሚለው ሃሳብ የውይይቱ መሰረተ ሃሳብ እንደሚሆን ይጠበቃል።
- ንቦች በክረምት ወራትና በዝናብ ወቅት መብረርና አበባ መቅሰም ስለማይችሉ ንብ አርቢዎች ስኳርና ዱቄት በቀፎአቸው አጠገብ ማስቀመጥ ያለባቸው መሆኑን እንዲረዱ ማድረግ መልካም ነው።
- ንብ በማነብም ማር፣ ሰምና የማር ሙጫ ማግኘት እንደሚቻል ይግለጹላቸው።
- ማር
  - መጠጦችን ለማዘጋጀት፣
  - ምግቦችን ለማጣፈጥ፣
  - መድሃኒት ለመቀመም፣
  - ለሽያጭ በማቅረብ ገቢን ማዳበርና ሌሎችም ጥቅሞች እንዳሉት ያስረዷቸው።
- ሌላው የንብ ውጤት የሆነው ሰም፡-
  - ሻማና ጧፍ ለመስራት፣
  - ቤት ለመወልወልና
  - ሰባራ እቃዎችን ለመጠገን እንደሚጠቅም ያሳውቋቸው።
- ንቦች እንደ ዝንብና የወባ ትንኝ አራት የእድገት ደረጃዎች (የህይወት ዑደት) አላቸው። እነሱም እንቁላል፣ እጭ፣ ሙሽሬ(ፑፓ) እና ጉልምስ (የተሟላ ንብ) በመባል እንደሚታወቁ ያስረዷቸው።
- ንቦች ማህበራዊ ነፍሳት እንደሆኑና በተናጠል የማይኖሩ መሆናቸውን እንዲሁም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ንቦች በአንድ ቀፎ ውስጥ በጋራ እንደሚኖሩ በማስረዳት ያጠቃልሉ።
- ትንንሽ እንስሳትን በተመለከተ ዝንብ፣ የወባ ትንኝ፣ አንበጣና የመሳሰሉት ነፍሳት ተመሳሳይ ውጫዊ የሰውነት አወቃቀር እንዳላቸውና ራስ፣ ደረትና የታችኛው ሰውነት ተብለው እንደሚጠሩ ይንገሯቸው።
- በራስ የሰውነት ክፍል ላይ አፍ፣ ዓይንና አቅጣጫ ጠቋሚ አንቴና የሚባሉ አካሎች ይገኛሉ። በነፍሳት ደረት ላይ ደግሞ ሶስት ጥንድ እግሮችና እንደየነፍሳቱ ዓይነት ሁለት ወይም አራት ክንፎች እንዳሉ፣ ሶስተኛው የታችኛው የሰውነት ክፍል እንደሚባልና የነፍሳት የመተንፈሻ ቀዳዳዎች (እስፓይራክልስ) እንዳሉበት ያስረዱአቸው።
- የእንስሳቱን (የነፍሳቱን) የሰውነት ክፍሎች አጉሊ መነፅርን በመጠቀም እንዲመለከቱና የተለያዩ ነፍሳት አካሎች ተመሳሳይነታቸውን እያወዳደሩ እንዲያጠኑ ይርዷቸው።

- በአጉሊ መነጽር ያዩትን የእነዚህን ነፍሳት ስዕል በመሳል ውጫዊ የአካል ክፍሎችን ለይተው እንዲያሳዩ ያድርጓቸው።
- ቀደም ሲል በትምህርት ቤቱ ቤተ ሙከራ የሚገኙ የተዘጋጁና የደረቁ ነፍሳት አካላት ካሉ ወይም ከትምህርቱ በፊት ቀደም ብለው እንዚህን እንስሳት በማድረቅ ማዘጋጀትና ተማሪዎቹ እንዲያዩ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።
- እንደሚታወቀው ዝንብ በቤት አካባቢ ቆሻሻ ባለበት ቦታ የምትራባ የነፍሳት ዓይነት ስትሆን ሶስት የአካል ክፍሎች እንዳሏት ፈሳሽ ምግብ በመምጠጥ የምትመገብበት ቀጭን የመምጠጫ ቱቦ ፕሮቦሲስ የሚባል አፍ ያላት መሆኑን በማብራራት ከተቻለ ተማሪዎቹ በአጉሊ መነጽር አማካይነት ለይተው እንዲያዩ ማድረግ የተሻለ ይሆናል። በተጨማሪም ሁለት ትልልቅ አይኖችና አንቴናዎችን እንዲያጤኑ ይርዷቸው
- በደረቷ ላይ ሶስት ጥንድ እግሮችና ሁለት ክንፎች እንዲሁም በታችኛው የሰውነት ክፍል ላይ የመተነፈሻ ቀዳዳዎች እስፓይራክልስ መኖራቸውን እንዲያስተውሉ ማገዝና በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን ስዕል እንዲመለከቱና በአጉሊ መነጽር ካዩት ጋር እንዲያወዳድሩ ያመቻቹላቸው።
- የወባ ትንኝም እንደ ዝንቦች ሶስት የአካል ክፍሎች (ራስ፣ደረትና ሰውነት) አሏት። ተማሪዎቹ በአጉሊ መነጽር ወይም በስዕሉ ላይ የተመለከቱትን አካሎች በማስተዋል ደም የምትመጥበትን ፕሮቦሲስ፣ ስድስት ረጃጅም እግሮችንና ሁለት ክንፎችን ለይተው እንዲያጠኑ ያበረታቷቸው።
- አንበጣም ሶስት የአካል ክፍሎች ካሏቸው ነፍሳት የሚመደብ ሲሆን ደረቱ ጠንካራ ነው። በደረቱ ላይም ስድስት እግሮች አራት ክንፎች እንዳሉት፣ የኋለኛዎቹ እግሮች ትልልቅና ለመዝለል የሚገለገልባቸው መሆናቸውን አንበጣውን ወደ ክፍል በማምጣት ወይም በቤተ ሙከራ ተዘጋጅቶ የተቀመጠ ካለ አካሎቹን በዝርዝር ለይተው እንዲያዩ መርዳት።
- አንበጣ ምግብ ለመመገብ የሚጠቀምበት የመንከሻና የመቆራረጫ አፍ ያለው መሆኑን ማስረዳት ከተቻለም በአጉሊ መነጽር አይተው እንዲለዩ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡
- አንበጣዎች መንጋ በመፍጠር በህብረት ሰብሎች ወዳሉበት አካባቢ በመብረር ሰብሎችንና ሌሎች እጽዋትን በመብላት ከፍተኛ ጥፋት እንደሚያደርሱ ያስረዷቸው።
- ንቦችን በተመለከተ ከላይ ከተጠቀሱት ትንንሽ እንስሳት ጋር በውጫዊ የአካል ክፍሎች ቢመሳሰሉም ለሰዎች ከፍተኛ ጥቅም እንደሚያበረክቱ ከዚህ በፊት ስለንቦች የተማሩትን በማስታወስ ያብራሩላቸው።
- ንቦች በህብረት የመኖር ተፈጥሮአዊ ልምድ ያላቸው ማግበራዊ ነፍሳት ሲሆኑ በአንድ ቀፎ የሚኖሩ ንቦች፡-
    - ንግስት ንብ፣
    - ድንጉል(ወንድ) ንብና
    - ሠራተኛ ንብ በመባል በሶስት የስራ ክፍፍል ተመድበው እንደሚኖሩ ይግለጹላቸው።

- ንግስቲቱ፣ድንጉል(ወንድ) እና ሠራተኛ ንቦች ምን ምን ስራ እንደሚያከናውኑ በቡድን የቤት ስራ ይስጧቸውና በአካባቢያቸው ትልልቅ ሰዎችን ጠይቀው እንዲረዱ ያድርጉ። ከዚያም ጠይቀው የተረዱትን ከእርስዎ ማብራሪያ ጋር በማዛመድ ንግስቲቱ ሴት ንብ እንቁላል እንደምትጥል፣ ድንጉል(ወንድ) ንብ ደግሞ ሴቷን ንብ በማጥቃት እንቁላል እንድትጥል የሚያደርግ እንደሆነና ሠራተኛ ንቦች በመማሪያ መፅሐፉ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች እንደሚያበረክቱና በሁሉም በጋራ እንደሚኖሩ ያስረዷቸው።
- እንደሌሎቹ ነፍሳት ንቦችም ሶስት የአካል ክፍሎች እንዳላቸውና የአበባ መቅሰሚያ ፕሮቦሲስ፣ሁለት ክንፎች እንዲሁም ስድስት እግሮች እንደሚገኙባቸው ይጥቀሱላቸው፡
- በመጨረሻም ከተማሪዎቹ ጋር በጋራ የትንንሽ እንስሳት የዝንብን፣ የወባትንኝን፣ የአንበጣንና የንብን ውጫዊ ክፍሎች በአጉሊ መነጽር በማየት የሶስቱ አካል ክፍሎቻቸው መመሳሰል፣ የእግሮቻቸው፣ የክንፎቻቸውና የመመገቢያ አፉቸውን ልዩነት በማጥናት ለመረዳት እንዲችሉና እንዲገነዘቡ በማድረግ ትምህርቱን ያጠቃሉ።

4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-
   - የለም አፈርና ለም ያልሆነ አፈር ናሙና፣
   - የችግኝ መደብ አዘገጃጀት የሚያሳይ ስዕል፣
   - የጓሮ አትክልት አተካከልና እንክብዳቤ የተግባር ክንዋኔ፣
   - የነፍሳት አካል ክፍሎችን የሚያሳይ ስዕል፣
   - የነፍሳት ሕይወተ ዑደት የሚያሳይ ስዕል፣
   - የትንንሽ እንስሳት ውጫዊ ክፍሎች ስእል።

5. **የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች፡-**
   - አፈር ለሰብሎች የሚሰጠውን ጥቅም ጠይቆ መረዳታቸውን መገምገም፣
   - የአፈር ዓይነቶችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣
   - ለምና ለም ያልሆነ አፈርን ለይተው እንዳወቁ ጠይቆ መረዳት፣
   - የችግኝ ማፍያ መደብ አዘገጃጀት ቅደም ተከተልን ዘርዝረው መናገራቸውን ማረጋገጥ፣
   - በመስመር መዝራትና በብተና መዝራት መካከል ያለውን ልዩነት እንዲገልፁ መጠየቅ፣
   - የተክሎችን እድገት ለመከታተል መደረግ የሚገባው ምን እንደሆነ መጠየቅ፣
   - በሰብሎች ላይ ጥፋት የሚያደርሱ ተባዮችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፣
   - የዝንብና የወባ ትንኝ የሕይወት ዑደት (የመዋለድ ዑደት)እንዲያስረዱ መጠያቅ፣

- የንብ አናቢነትን ጥቅም የመግለጽ ችሎታቸውን ጠይቆ መረዳት
- የማር ጥቅሞችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅና መገምገም
- አጉሊ መነፅርን በመጠቀም የነፍሳትን ውጫዊ አካላት ከስዕል ላይ ማመልከት እንደሚችሉና ስም ስማቸውን እንዲናገሩ መጠየቅ

## የመልመጃ 3.1 መልሶች

ሀ/ 1. እውነት

6. ሃሰት

2.ሃሰት

7.

እውነት

3.እውነት

4.እውነት

5. ሃሰት

8. ሃሰት

9. እውነት

10. እውነት

ለ/ 1. ለ

5. ለ

2. መ

6. ለ

3. ለ

7. ሀ

4. ሐ

8. መ

ሐ/ 1. አራት የእድገት ደረጃዎች ፡ ለምሳሌ ዝንብ፣ የወባ ትንኝ፣ ቢራቢሮ፣ ንብ የመሳሰሉት ሶስት የእድገት ደረጃዎችም ያላቸው አሉ። ምሳሌ አንበጣ

2. ሰብሎችን ማረም አረሞች በሰብሎች ውስጥ በቅለው ውሃንና ማእድናትን ስለሚሻሙ ነው
3. ንብ ማርባት-የማር፣የሰምና የማር ሙጫ ምርቶችን ለማግኘት ይጠቅማል
4. ዝንቦች ጀርሞችን ከቆሻሻ ቦታዎች ወይም ከእንስሳት ዓይነ ምድር በእግሮቻቸውና በክንፎቻቸው አማካይነት ወደ ተዘጋጀ ምግብና ወደ ጤነኛ ሰው ሰውነት ያስተላልፋሉ፡
5. እህልን በማከማቻ ውስጥ ለማስቀመጥ የእህሉን መከማቻ ጎተራዎችና መጋዘኖች ማፅዳትና የፀረ-ሰብል ተባዮችን መድሃኒት መርጨት ያስፈልጋል።

## **3.2** የአካባቢው ኢንዱስቲሪ ምርቶች

የተመደበው ጊዜ **12** ክፍል ጊዜ

1. ዝርዝር ዓላማዎች፡-ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ
   - በአካባቢያቸው የሚመረቱ ምርቶችን ዝርዝር ያውቃሉ
   - ለአካባቢያቸው ምርቶች ፍላጎት ያሳያሉ
   - በሻጭና ገዥ መካከል ያለውን ቁርኝት ይገልጻሉ፣ ያስረዳሉ።
2. ዝርዝር ይዘቶች፡-
   - በአካባቢያችን የሚመረቱ ምርቶች ዓይነት
   - ገዥና ሻጭ ያላቸው ግንኙነት

መግለጫ

በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ምርቶች ይመረታሉ፡ ገበሬዎች የግብርና ምርቶችን (የምግብ ሰብሎችን፣ አትክልትና ፍራፍሬዎችን) በማምረት ለቤተሰቦቻቸው ኑሮ መሰረታዊ ፍላጎትና ለሽያጭ ያውላሉ። ቡና፣ ማር፣ ወተት፣ በርበሬ እንዲሁም የእንስሳት ውጤቶች የግብርና ምርቶች ናቸው፡

ሌሎች ሰዎች ደግሞ በጎጆ ኢንዱስትሪ ተሰማርተው በእንጨት ስራ፣ በሸክላ፣በብረታብረት፣ በጌጣጌጥ፣ በስፌትና በሽመና ስራ የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ለገበያ ያቀርባሉ።

ምርቶች በሱቆችና በገበያዎች ይሸጣሉ። በምርት ሻጭና ገዥ መካከል የጠበቀ ግንኙነትም ይፈጠራል። ገዥዎችም የአካባቢያቸውን ምርቶች ለመግዛት ፍላጎትና ልምድ ማዳበር ይገባቸዋል።

3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚመረቱ ምርቶችን ዘርዝረው እንዲናገሩ በመጠየቅና በትምህርቱ ውስጥ የሚያገኟቸውን ቁልፍ ቃላት በማስተዋወቅ ትምህርቱን ይጀምሩ። በአካባቢያቸው የሚመረቱ ምርቶችን እንደየአካባቢው ሁኔታ ሊጠሩ ይችላሉ ይቀበሏቸው። ከዚያም በማስከተል ሰዎች የተለያዩ ስራዎችን በመስራት ኑሮአቸውን እንደሚመሩ፣ ገበሬዎች የግብርና ምርቶችን ሲያመርቱ ሌሎች ሰዎች ደግሞ በጎጆ ኢንዱስትሪ ስራ ተሰማርተው ልዩ ልዩ የምርት ውጤቶችን እንደሚያመርቱ ያስረዷቸው
- የግብርና ሰዎች
    - የምግብ ሰብሎችን፣
    - የቡና፣
    - የማር፣
    - የወተት፣
    - የበርበሬ እንዲሁም
    - የእንስሳት ውጤቶች የቆዳና ሌጦ ምርቶችን በማምረት ለቤተሰቦቻቸው ፍጆታ ወይም በአገር ውስጥና በውጭ አገር ገበያዎች ሸጠው ገቢ ማግኘት እንደሚችሉ ይግለጹላቸው።
- በጎጆ ኢንዱስትሪ የማምረት ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎችም በተለያዩ ሙያ ዘርፍ ማለትም በሸክላ፣ በእንጨት፣ ቡብረታብረት፣ በሸማና በጌጣጌጥ ስራ ለህብረተሰቡ የሚጠቅሙ የተለያዩ ምርቶችን እንደሚያመርቱ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ በዝርዝር በቀረበው መሰረት ምሳሌዎችን በመጥቀስ ያብራሩላቸው።
- ተማሪዎቹን በግብርናም ሆነ በጎጆ እንዱስትሪ ከሚመረቱ የምርት ዓይነቶች የትኞቹ በአካባቢያቸው እንደሚመረቱ ዘርዝረው በመመዝገብ እንዲያመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው
- ገዥና ሻጭ ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ተማሪዎቹ በትምህርት ቤታቸው አካባቢ የተመረቱ ምርቶች የት የት አንደሚሸጡ ይጠይቋቸው። ሃሳባቸውንም ይቀበሏቸው። ለሽያጭ የሚቀርቡት በሱቆችና በገበያዎች መሆኑን ያብራሩላቸው። የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር ሱቆችም የተለያዩ ምርቶችን ገዝተው በማቅረብ ለሸማቾች በተመጣጣኝ ዋጋ እንደሚሸጡ ያስረዷቸው።
- ምርቶችን በሱቆችና በገበያዎች በሚሸጡና በሚገዙ ሰዎች መካከል የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን፣ ምርቶች የሚጠቀሙ ደግሞ በአካባቢው ለሚመረቱ ምርቶች የመግዛት ፍላጎት በማዳበር በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት መጠናከር እንዳለበት እንዲረዱ ይግለፁላቸው።
- በመጨረሻም የቀረበው ጥያቄ በተለያዩ ቦታዎች የሚመረቱ ምርቶች በንግድ ሥራ በተሠማሩ ሰዎች አማካይነት ወደ ሱቆችና ገበያዎች ቀርበው፣ምርቱን ገዝተው የሚጠቀሙ ሰዎች በአካባቢያቸው በቅርብ አግኝተው ለመግዛት በመቻላቸው ይጠቀማሉ። ሻጮችም

ምርቶችን በመሸጥ ይጠቀማሉ። ስለዚህ በተማሪዎቹ አካባቢዎች ቤተሰቦቻቸው ወይም ጐረቤቶቻቸው ወይም የሚያውቋቸው ሰዎች ምርት በማምረትና በማከፋፈል ህብረተሰቡ በቀላሉ እንዲገዛ በማድረግ ወይም ደግሞ እነሱ እራሳቸው የቀረቡትን ምርቶች ከሱቅና ከገበያዎች የሚገዙ ሊሆኑ ስለሚችሉ የመደጋገፍ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ እንደሆነ በማስረዳት ትምህርቱን ያጠቃልሉ

4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-

- በትምህርት ቤት አካባቢ የሚመረቱ ምርቶችንና
- በተለያዩ ጐጆ ኢንዱስትሪዎች የሚመረቱ ምርቶችን አሠራር መጐብኘት

## 5. የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው የሚመረቱ ምርቶችን ዘርዝረው እንዲናገሩ መጠየቅና መገምገም
- በገዥና በሻጭ መካከል ያለውን ግንኙነት መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ተማሪዎች አጥጋቢ ብቃት ላይ ከተቀመጡት መስፈርቶች በላይ የሠሩ እንደሆነ መሸለምና ሥራቸውንም እንዲቀጥሉበት ማበረታታት
- ከመስፈርቶቹ በታች የሠሩ እንደሆነ ተጨማሪ ዕርዳታ በማድረግ ለጥሩ ደረጃ ማድረስ ያስፈልጋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

ሀ/ 1. እውነት 5. እውነት

2. እውነት 6. ሃሰት

3.ሃሰት 7. ሃሰት

4.እውነት 8. ሃሰት

ለ/ 1. ሠ 6. ሐ

2.ቀ 7. መ

3.በ 8. ረ

4.ለ 9. ተ

5.ሀ 10. ቸ

ሐ/ 1. ለ

5. ሀ

2. መ

6. መ

3 ሀ 7. ሐ

4.ሐ 8. ለ

መ/ 1. በመስመር አዘራር ዘዴና ቡብተና አዘራር ዘዴ

2. ማር፣ሰምና የማር ሙጫ

3. ጉልምስ

4.ደም

ሠ/ 1. እንቁላ፣እጭ፣ ሙሽሬና ጉልምስ ናቸው

2. በሰብሎች ውስጥ ያልተፈለጉ ሌሎች /አረሞች ምግብና ውሃ ስለሚሻሙ ነው።

3. ማር፣ሰምና የማር ሙጫን ያስገኛሉ

4. እጭ ነው

5. ዝንብ በሽታ የሚያስከትሉ ጀርሞችን በመሸከምና በማስተላለፍ ጤናማ ሰውን በበሽታ እንዲታመም ስለምታደርግ ነው
6. ባህላዊና ዘመናዊ የንብ ቀፎዎች ናቸው
7. ንግስት፣ድንጉል/ወንድ ንብ/እና ሠራተኛ ንብ ናቸው።
8. የወባ ትንኝ ከታመመ ሰው ደም ከወባ በሽታ ጀርሞች ጋር በመምጠጥ ወደ ጤነኛ ሰው ስለምታስተላልፍ ነው።
9. ጌጣ ጌጦች፣ ጠረጴዛ፣አልጋ፣የልብስ ውጤቶች፣የቆዳ ውጤቶች /ቀበቶ ቦርሳ/፣የሸክላ ቁሳቁሶች /ጀበና እንስራ የሸክላ ድስት/እና የመሳሰሉት ናቸው።

# ክፍለ ትምህርት አራት

# ክልላችን

የተመደበለት ጊዜ **55** ክፍለ ጊዜ

*መግቢያ*

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የክልላችን መገኛ፣ የክልሉ ዋና ዋና የመሬት አቀማመጥ፣ ክልላዊና ብሄራዊ ሰንደቅ ዓላማዎች፣ አስተዳደራዊ መዋቅሮች፣ቅርስና በክልሉ አገር ወዳድነት የሚሉ ይዘቶች ተካተዋል።

መምህር! በእያንዳንዱ ይዘት ሥር የተነደፉትን ዓላማዎች ለማሳካት፡

1. በመማሪያው መጽሐፍ ውስጥ በቀረቡት ፍሬ ሀሳቦች መልመጃዎችና ተግባራዊ ክንዋኔዎች በመደገፍ ተማሪዎችን አሳታፊ በሆነ መልኩ ትምህርቱን ማስተላለፍ
2. በማስተማሪያው መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡልዎትን የመማር ማስተማር ክንውን መግለጫዎችን፣ በትምህርት መርጃነት የቀረቡትን ቁሳቁሶችና ሥዕሎችን፣ እንደዚሁም የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ የራስዎን ፈጠራ አክለውበት ማስተማር ይጠበቅብዎታል።

## አጠቃይ ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ፡-

- ክልላቸውን ከአጎራባች ክልሎች እና አገሮች ጋር በማገናኘት ይለያሉ።
- የክልላቸውን ዋና ዋና የመሬት አቀማመጥ ይለያሉ ።
- የብሄራዊና ክልላዊ ሰንደቅ ዓላማዎችን ቀለማት ይገልፃሉ።
- የክልሉን የመስተዳድር መዋቅርና ዋና ዋና መሥሪያ ቤቶችን ይገልፃሉ።
- የክልሉን ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶችን ይሰበስባሉ።
- የክልሉን አርበኞችና አገር ወዳዶች ሥም ይዘረዝራሉ ያገኙትንም ውጤት በማድነቅ ተተኪ ለመሆን ይወስናሉ።
- ሳይንሳዊ ክሂሎችን ተግባራዊ በማድረግ ያሳያሉ፡-
- አካባቢን በመመልከት ፣በመገንዘብ፣በመመደብ ፣በመጠየቅ፣ትርጉም በመስጠት፣ሀሳብ ለሀሳብ በመለዋወጥና በመተባበር ይሰራሉ።

## 4.1. የክልላችን መገኛ

የተመደበለት ጊዜ 5 ክፍለ ጊዜ

1. ዝርዝር ዓላማዎች

   ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ

   - ክልላቸውን ከአጎራባች ክልሎችና አገሮች ጋር በማገናኘት ያሳያሉ

2. ዝርዝር ይዘቶች

   - ክልላችንና አጎራባች ክልሎች

3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

መምህር፦ ትምህርቱን ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ከተገኘ ከእንጨት የተሠራ የአቅጣጫ መጠቆሚያ አሊያም ሥዕል አጎልተው ያዘጋጁ። ወደ ክፍል እንደገቡም ተማሪዎች ስለ ክልላቸውና ስለሌሎቹም ብሄራዊ ክልሎች ያላቸውን ግንዛቤ ለመረዳት ጥያቄ ይጠይቋቸው። ኢትዮጵያ በስንት ክልሎች እንደተከፈለች፣ የክልሎቹ ስሞች እነማን እንደሆኑ ፣ ተማሪዎቹ በየትኛው ክልል እንደሚኖሩ፣ ከክልላቸው ጎን የሚገኙ አጎራባች ክልሎችን ወዘተ መጠየቅ ይችላሉ ።

ከዚህ በመነሳት በካርታ ተደግፈው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ክልሎችን ያብራሩላቸው። ከዘጠኙ ክልሎች አንዱ ክልላችን መሆኑንና መጠሪያ ስያሜውም የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መሆኑን ይግለፁላቸው። ይህ ሲሆን ተማሪዎቹ በካርታው ላይ ክልላቸውን

1. በቅርጹ
2. በአቅጣጫው
3. በአጎራባቾቹ አማካይነት መለየት እንዲችሉ ይምሯቸው ። ተግባራዊ ክንዋኔውን ተረድተውት እንዲሰሩ ይምሯቸው። ተማሪዎቹን በቡድን ይከፋፏቸውና ለእያንዳንዱ ቡድን በመማሪያ መጽሐፋቸው የተጠቆሙትን ቁሳቁሶች እንዲያዘጋጁ አስቀድመው ይንገሯቸው ። ቀለማቱን ከአካባቢው ማዘጋጀት እንደሚችሉም ሀሳብ ይስጧቸው ። ካርታውን ከሠሩ በኋላ የደ.ብ.ብ.ህ.ክልልን ምልክት አድርገውበት የመረጡትን ቀለም እንዲቀቡና አጎራባቾቹን የተለያዩ ቀለማት በመቀባት እንዲለዩዋቸው ያድርጉ ። የኬንያን ድንበርና የደቡብ የሱዳንን ድንበር እንደዚሁ ከክልሎቹ የተለዩ ቀለማትን ሊቀቧቸው ይችላሉ። በቀለም አጠቃቀም በካርታ አሳሳል ወዘተ እገዛ ሊያደርጉላቸው ይገባል። ተማሪዎቹ የሠሩትን (የደ.ብ.ብ.ህ.ክልልና አጎራባች ክልሎች) አወዳድረው የተሻለውን በክፍላቸው ውስጥ እዲለጥፉ ያበረታቷቸው።

4. የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች

   - የኢትዮጵያ ብሄራዊ ክልሎች ካርታ

- ❖ የተለያዩ ቀለማት
- ❖ ወረቀት
- ❖ ላጲስ
- ❖ ማጣበቂያ /ሙጫ/

**5.** የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- ❖ መምህር፡- ተማሪዎችዎ የሠሯቸውን ሥራዎች ተከታታይ ምዘና በማድረግ ውጤቶቻቸውን መለካት ያስፈልጋል።
- ❖ ተማሪዎቹ አጥጋቢ ብቃት ላይ ናቸው ለማለት የሚቻለው ክልላቸውን ከአጎራባች ክልሎች ጋር በማያያዝ ያሳዩ እንደሆነ ነው።

ስለዚህ ተማሪዎቹ ክልላቸውን በመጠን ፣ በቅርፅ፣ በአንፃራዊ አቅጣጫ እና በአጎራባቾቹ አማካይነት መለየታቸውን ይፈትሹ።

ከአጥጋቢ ውጤት በላይ ያመጡትን ተማሪዎች ማበረታታትና ለላቀ ውጤት እንዲተጉ ማድረግ ይገባዎታል። ከተፈለገው ውጤት በታች ያመጡት ተማሪዎች ተጨማሪ ጊዜ ወስደው የማብቃት ሥራ መሥራት ይጠበቅብዎታል ።

## የመልመጃ **4.1** መልሶች

1. የደ.ብ.ብ.ህ.ክልል ካርታ ከነአጎራባቾቹ ከተሠራ በኋላ ቆርጦ በማውጣት ስፋትን ማወዳደር።
   - አነስተኛ ሰፋት ያለው ጋምቤላ
   - መካከለኛ ስፋት ያለው የደ.ብ.ብ.ህ.ክልል
   - ትልቅ ሰፋት ያለው የኦሮሚያ ክልል
2. የውይይቱ መቋጫ መሆን የሚገባው
   የአጎራባች ክልል ህዝቦች መኖር የሚገባቸው

- ተቻችለው
- ተፈቃቅረው
- በመረዳዳትና በመተባበር ነው።

## 4.2. ዋና ዋና የመሬት አቀማመጥ

የተመደበለት ጊዜ- **10** ክፍለ ጊዜ

### 1. ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ፡-

- የክልላቸውን ዋና ዋና የመሬት አቀማመጥ ይለያሉ
- ዋና ዋና የመሬት አቀማመጥ ምሳሌዎችን ይሰጣሉ

### 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ተራሮች
- ወንዞች
- ሀይቆች

### 3. የመማር - ማስተማር ክንውኖች

መምህር፡- ተማሪዎችዎ ስለክልላቸው መገኛ የተማሩትን ትምህርት ፍሬ ሀሳብ በመከለስ ትምህርቱን ያያይዙ። ቀጥሎም በየንዑስ ርእሱ ሥር የተዘጋጁትን ወይም እርስዎ የሚያዘጋጇቸውን የመክፈቻ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ወደ ማስተማሩ ይግቡ። በሚሰጧቸው ሀሳቦችም መነቀፍ አይገባቸውም። ወይም "ልክ ነው!" "ልክ አይደለም" ሳይሉ ወደ ትክክለኛ የትምህርቱ ገለፃ ይግቡ።

ተራሮች በሚለው ይዘት ሥር በመማሪያው መጽሐፍ እንደተገለፀው እንደፕላቶ፣ ኮረብታና ተራራ ሰንሰለት ያሉት ከፍተኛ ምድሮች ገብተዋል። ይህ ሊሆን የቻለው ተማሪዎች ከተጠቀሱት መልከአ ምድራዊ ገጽታዎች ጋር ቅርበት ስለሚኖራቸው በየአካቢያቸው ስለሚያዩዋቸው ለንፅፅር ቢቀርቡ ትምህርቱን ያቀለዋል በሚል ነው። በእርስዎ በኩልም ስለመልከአምድር ሲያስተምሩ ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን ከክፍል ውጭ በርቀት እንኳ ቢሆን የመልከአምድሩን አቀማመጥ ማየትና ማድነቅ በሚችሉበት ሁኔታ በጉብኝት መልክ ቢሆን ይመረጣል ። ተማሪዎች ከመስክ እንደተመለሱ ፕላቶ ፣ኮረብታና ተራራ በቅርፅ ወይም በከፍታ ወይም በከፍታና በቅርፅ ሊለዩ እንደሚችሉ ያስረዷቸው ። ከዚህ ጋር በማስታከክም በደ.ብ.ብ.ህ.ክልል ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ተራሮችን ስሞች እየጠቀሱ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ያበረታቷቸው።

ወንዞችን በሚመለከት በክልላችን በርካታ ወንዞች እንዳሉና ስሞቻቸውን ከማወቃቸው በፊት በአካባቢያቸው ካሉት ወንዞች ቢነሱ ይመረጣል።ተማሪዎቹ ስለወንዞች ጥቅምም በሥፋት እንዲወያዩ ያድርጉና ማስተካከያና ተጨማሪም ይስጧቸው። ከወንዞቹ ጋር ተያይዘው የተነሱት የወንዞች ሸለቆና የሰምጥ ሸለቆ ናቸው። ተማሪዎቹ የወንዞች ሸለቆ ወንዞች መሬቱን እየበረበሩ የሚፈጥሩት ጎድጓዳ ሸለቆ መሆኑንና ሥምጥ ሸለቆ ስፋት ያለው ዝቅተኛ ቦታ መሆኑን እንዲረዱ ያድርጉ። የስምጥ ሸለቆ ምሳሌ የጨው ባህር ስምጥ እንደሆነም ይግለፁላቸው ።

ሀይቆች በክልሉ ውስጥ የሚገኙት ሀይቆች የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች እና የስምጥ ሸለቆ ያልሆኑ ሀይቆች ናቸው። በዚህ ክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የሰምጥ ሸለቆ ሀይቆችን ማስተዋወቁ በቂ ስለሚሆን ስለ ሀዋሣ ሀይቅ ፣ ስለ አባያ፣ጫሞና ጨው ባህር ሀይቆች መጥቀሱ ይበቃል። አያይዘውም ስለሀይቆቹ ጥቅም ተማሪዎቹ እንዲወያዩና እንዲዘረዝሩ ያበረታቷቸው ። ቀደም ሲል በተፈጥሮ ሀብቶች ውስጥ ስለውሃ የተማሩትን አስታውሰው ትምህርቱን ያያዙላቸው።

ተግባራዊ ክንዋኔውን በተመለከተ የቅርብ ክትትልና እገዛ ያስፈልጋቸዋል። በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረበውን የመልክአምድር ካርታ እርስዎ አጎልተው ቢያቀርቡላቸው ከተቻለም በአካባቢው ከሚገኙት የግብርና መሥሪያ ቤቶች ትብብር በመጠየቅ መጽሀፍ ውስጥ የቀረበውን ዓይነት ወካይ የመሬት አቀማመጥ በመጠቀም ተማሪዎቹ ሥዕሉን ስለው ቀለማት መቀባት እንዲችሉ ይርዷቸው ።

ቀለማቱ ቡኒ - ለከፍተኛ ምድር ( ለተራራ)

ውሃ ሰማያዊ - ለሀይቆችና ሌሎች ውሃማ አካላት

ብጫ ቀለም - ለዝቅተኛ ቦታዎች

አረንጓዴ -ለእፅዋት መጠቀም እንዳለባቸው ያስተምሯቸው። የእነዚህ ቀለማት የስምምነት ጉዳይ እንጂ ከመሬት አቀማመጥ ጋር የተለየ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ማሳወቅ ይኖርብዎታል።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ❖ የክልሉን ዋና ዋና የመልክአምድር ዓይነቶች የያዘ ወካይ ካርታ
- ❖ ወረቀት ፣ እርሳስ፣ ላጲስ ወዘተ
- ❖ የተለያዩ ቀለማት (ከአካባቢ የሚዘጋጁም ይኖራሉ )

- ቡኒ ቀለም

- ውሃ ሰማያዊ ቀለም

- ብጫ ቀለም

- አረንጓዴ ቀለም

- የደ.ብ.ብ.ህ .ክልል ተፈጥሮአዊ ካርታ

## 5. የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎች

- በእያንዳንዱ ይዘት አኳያ የተነደፉትን ዓላማዎች ለማሳካት ተከታታይ ምዘና በማድረግ ተማሪዎች በጥሩ ብቃት ላይ መገኘታቸውን መገምገም ያስፈልጋል። ተማሪዎች አጥጋቢ ብቃት ላይ ናቸው ለማለት የሚቻለው የክልሉን ዋና ዋና የመሬት አቀማመጥ /መልካአምድራዊ ገጽታዎች/ መለየትና ምሳሌ መስጠት የቻሉ እንደሆነ ነው። በዚህም መሠረት ከአጥጋቢ ውጤት በላይ ያስመዘገቡትን ተማሪዎች ምስጋናና ሽልማትም በመስጠት ለላቀ ውጤት እንዲበረታቱ እንደዚሁም ከአጥጋቢ ውጤት በታች ያስመዘገቡትን ተማሪዎች የትምህርት አሰጣጥን ዘዴ ቀይረው ተጨማሪ ጊዜ በመውሰድ የማብቃት ሥራ መስራት ይጠበቅብዎታል።

### የመልመጃ 4.2 መልሶች

ሀ) 1. ሀሰት

2. እውነት

3. እውነት

ለ) 1. ሐ

3. ሀ

2. መ

4. ለ

ሐ. 1. ሐ

4.ሀ

2. ለ 5. ለ

3. ሀ

## 4.3 ክልላዊና ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማዎች

የተመደበለት ጊዜ- **5** ክፍለ ጊዜ

## **1.** ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ፡-

- የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማን ቀለማትና ዲዛይን ይለያዩ
- የክልላቸውን ሰንደቅ ዓላማ ቀለማትና ዲዛይን ይለያዩ

## **2.** ዝርዝር ይዘቶች

- የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀለማትና ዲዛይን
- የደ.ብ.ብ.ሕ.ክልል ሰንደቅ ዓላማ ቀለማትና ዲዛይን

## **3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

ተማሪዎችን በቡድን በቡድን ይክፈሏቸው።

በትምህርት ቤት ውስጥ ሰንደቅ ዓላማ የሚሰቀለውና የሚወርደው መቼ እንደሆነ በመጠየቅ ወደ ውይይት ያስገቧቸው። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣና ሲወርድ የሚዘመረውን ብሄራዊ መዝሙር በክፍል ውስጥ ቆመው እንዲዘምሩ ያድርጉ። ቆመው የዘመሩት ወይም ተቀምጠው ያልዘመሩት ለምን እንደሆነ ይጠይቋቸው። ተማሪዎቹ በየቡድኖቻቸው ተግባራዊ ክንዋኔውን እንዲሰሩ ይምሯቸው ። እዚህ ላይ ተማሪዎቹ አስቀድመው ተዘጋጅተው እንዲመጡ ከወዲሁ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ቡድኖቹ ስለሰንደቅዓላማዎቹ ተወያይተው የውይይቶቻቸውን ፍሬሀሳቦች እንዲለዋወጡ ከአደረጉ በኋላ ስለ ሰንደቅ ዓላማ ምንነትና አስፈላጊነት ያስረዷቸው።

## የማብራሪያ ሀሳቦች

ሰንደቅ ዓላማ የአንድነትና የልአላዊነት ምልክት ነው። ሉአላዊነት ሲባል አንዲት ሀገር ራሷን በራሷ ያለምንም ጣልቃ ገብነት የምታስተዳድር መሆኗን የሚገልፅ ነው። ይህም ሉአላዊነት የሚረጋገጠው አገሪቷ የራሷ ሰንደቅ ዓላማ ሲኖራት ነው።

አንድነት ሲባል በአንድ ሀገር ህዝቦች መካከል የሚፈጠር አንድነት ማለት ነው። አንድነት ያላቸው ህዝቦች፡-

❖ ብሄራዊ ስሜት ያድርባቸዋል።

- ❖ የሀገር ፍቅር ይኖራቸዋል
- ❖ ለዜጎች የመቆርቆር ስሜት ያሳያሉ
- ❖ ተቻችለውና ተፈቃቅረው ይኖራሉ
- ❖ ሀገራቸውን ከጠላት በጋራ ይከላከላሉ
- ❖ ሀገራቸውን ለማልማት በጋራ ይነሳሉ ወዘተ

መምህር፡- ተማሪዎች ለሰንደቅ ዓላማ በመቆምና በማክበር ብሄራዊ መዝሙሩንም በመረዳት ለአንድነት እንዲቆሙ ኮትኩቶ ማሳደግና ማስተማር ያስፈልጋልና በዚህ መንፈስ ይቅረጿቸው።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ
- የደ.ብ.ብ.ህ.ክልል ሰንደቅዓላማ

## 5. የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎች

መምህር! በእያንዳንዱ ይዘት አኳያ የተነደፉት ዓላማዎች መሳካታቸውን ለመከታተል ተከታታይ ምዘና አድርገው ተማሪዎች በጥሩ ብቃት ላይ መገኘታቸውን ያረጋግጡ። ተማሪዎች ጥሩ ብቃት ላይ ናቸው ለማለት የሚቻለው የብሄራዊና የክልሉን ሰንደቅ ዓላማዎች ቀለማት ለይተው መናገር የቻሉ እንደሆነና የሰንደቅዓላማን አስፈላጊነት ማስረዳት ሲችሉ ነው። በዚህ መሠረት ተገምግመው ከጥሩ ብቃት በላይና በጥሩ ብቃት ላይ ያሉትን በማበረታታት ለበለጠ ውጤት ማዘጋጀት ይኖርብዎታል። እንደዚሁም ከበቂ ችሎታ በታች የሆኑትን ተማሪዎች ለመርዳት ተጨማሪ ጊዜ ወስደው የማስተማር ዘዴዎን ቀይረው የማብቃት ሥራ እንዲሠሩ ይጠበቃሉ።

## የመልመጃ 4.3 መልሶች

ሀ) 1. ሃሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሃሰት

ለ) 1. በመስከረም ወር ነው
2. ሰማያዊ ነጭ፣ ቀይና ጥቁር

3. ሰንደቅ ዓላማ የሚያስፈልገን የሠላም፣የአንድነትና የሉአላዊነት ምልክት ስለሆነ ነው።

## 4.4. አስተዳደራዊ መዋቅሮች

### የተመደቡበት ጊዜ - 10 ክፍለ ጊዜ

**1.** ዝርዝር ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ

- የክልሉን አስተዳደራዊ መዋቅሮች ይተነትናሉ
- የክልሉን ዋና ዋና ተቋማት ቤቶች ይዘረዝራሉ
- የክልሉን ዋና ዋና ተቋማት ቤቶች ተግባራት ይዘረዝራሉ

**2.** ዝርዝር ይዘቶች

- አስተዳደራዊ መዋቅሮች
- ዋና ዋና ተቋማት

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

መምህር ያለፈውን ትምህርት ፍሬ ሀሳቦች ያስታውሷቸው

ሀ. በዚህ አስተዳደር ይዘት ሥር የተቀመጡትን የማነቃቂያ/የመከፈቻ/ ጥያቄዎች እና ሌሎችንም በማቅረብ ትምህርቱን ያስጀምሩ፣ ያወያዩ። ይህን ርእስ ሲያስተምሩ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ክልሎች ካርታና የደ.ብ.ብ.ህ.ክልል ካርታ እንዳይለዩዎት በ4.1 እና በ4.3 ንዑስ ይዘቶች ውስጥ የቀረቡትን ፍሬ ሀሳቦች እንዲያስታውሱ ይምሯቸው። ቀጥለውም የክልሉን የሥልጣን አወቃቀር በማንሳት ለማስተማር በቅድሚያ የሥልጣን ተዋረዱን የሚያሳይ በሰሌዳ ላይ በትልቁ ይሳሉላቸው። ወይም በሰፊ ወረቀት ላይ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ እንደተመለከተው ይሳሉና የሥልጣን ተዋረዱን ከላይ ወደታች ግንኙነታቸውን ያስረዱ። ከፍተኛው የሥልጣን እርከን የክልል ምክር ቤቱ ነው ። ቀጥለው ዞን፣ልዩ ወረዳዎችና የከተማ አስተዳሮች በእኩል የሥልጣን እርከን ላይ ይገኛሉ።የከተማ አስተዳደር ወደ ወረዳ ወይም ክፍለ ከተማ እና ወደ ቀበሌ ፣ ዞኖች ወደ ወረዳና ቀበሌ እንደዚሁም ልዩ ወረዳዎች ወደ ቀበሌ ሥልጣኖቻቸውን በማውረድ የአስተዳደር አገልግሎት ይሰጣሉ።

ክልሉ በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች ሊዋቀር ያስፈለገበት ምክንያት፡-

1. ለአስተዳደር እንዲመች
2. የልማት ሥራዎችን ለመዘርጋት ቀልጣፋ አሠራር እንዲኖርና
3. ለህዝብ አገልግሎትን በቀላሉ ማዳረስ ተብሎ ነው ብለው ይግለፁላቸው። በአካባቢዎ ባሉት ምሳሌዎች እየተጠቀሙ ያስረዱ። ማህበራዊ አገልግሎት እንደ ጤና፣ ትምህርት፣ መንገድ ሥልክ ወዘተ የመሳሰሉትን ያካትታል ።

ተማሪዎች ከሚያውቁት የቀበሌ አስተዳደር በመነሳት በቀበሌው ሥር ያሉትን አደረጃጀቶች እያነሱ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ይርዷቸው። ቀበሌ በገጠሩም ሆነ በከተማው ጥበቃ /ፖሊስ/ ፣ ማህበራዊ ፍርድ ቤት፣ጽ/ቤት እና የልማት ኮሚቴዎች ወዘተ ይኖሩታል።

**ለ)** ዋና ዋና ተቋማት በሚለው ርእስ ሥር መንግታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተካተዋል። ተቋማት የመንግሥት፣ የግል እና የህዝብ ሊሆኑ ይችላሉ። እያንዳንዳቸው ለተለያዩ ዓላማዎች (አገልግሎቶች) ይቋቋሙ እንጂ ዓላማቸው ህዝብን ለማገልገል እንደሆነ ለተማሪዎች ያብራሩላቸው ። ተማሪዎች በክልሉ ርእሰ ከተማም ሆነ ከከተማው ውጭ ተቋቁመው አገልግሎቶች የሚሰጡት ድርጅቶችን /የሚያውቋቸውን/ እንዲዘረዝሩና ከስሞቻቸው ጋር የሚሰጡትን ጥቅም እንዲጠቅሱ ያበረታቷቸው።

## 4. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- የደ.ብ.ብ.ህ .ክልል ፖለቲካዊ ካርታ
- የኢትዮጵያ ብሄራዊ ክልሎች ካርታ
- የተቋማት ሥዕሎች

እነዚህን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከቀበሌና ወረዳ ጽ/ቤቶች ለማግኘት ይሞክሩ ። ይህ ካልተቻለ በመማሪያ መጽሀፍ ላይ ያሉትን አሳድገው በማንሳት ይጠቀሙ ።

## **5.** የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎች

ተማሪዎች የሚሰሯቸውን ሥራዎች በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ( ከተነደፈው ዓላማ አኳያ) ተከታታይ ምዘና በማድረግ በጥሩ ብቃት ላይ መገኘታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅብዎታል። ተማሪዎች በአጥጋቢ ብቃት ላይ ናቸው ለማለት የሚቻለው

1. የክልሉን የመንግሥት አስተዳደር አወቃቀር አውቀው ህዝቡ የአስተዳደር ግልጋሎት እንዴት እንደሚያገኝ ሲያስረዱ ፣
2. ዋና ዋና የመንግሥትና የመንግሥት ያልሆኑ ተቋማት ምን ምን ተግባራት እንደሚያከናውኑ /ሥራቸውን/ መለየት የቻሉ እንደሆነ ነው። በዚህ መሠረት ሲገመገሙ ተማሪዎቹ ከአጥጋቢ

ውጤት በላይ እና አጥጋቢ  ውጤት በታች ያገኙ ሊሆኑ ይችላሉ ። አጥጋቢና ከአጥጋቢ በላይ ውጤት ያስመዘገቡትን  ወደ ላቀ ውጤት እንዲሻጋገሩ ማመስገንና  መሸለም።  ከአጥጋቢ ውጤት በታች የሆኑትን የማስተማር  ዘዴዎን  ቀይረው የማብቃት ሥራ  እዲሰሩ ይጠበቃሉ።

## የመልመጃ 4.4 መልሶች

ሀ/ 1. ሃሰት 4. እውነት

2. እውነት 5. ሃሰት

3. ሃሰት

ለ/ 1.መ 4. ሠ

2. ሀ 5. ረ

3. ለ

ሐ. 1. ሀ

2. ሐ

3. ለ

## 4.5 ቅርሶች

የተመደበለት ጊዜ -   **15** ክፍለ ጊዜ

1. ዝርዝር  ዓላማዎች

ተማሪዎች  ይህንን ትምህርት  ተምረው ሲያጠናቅቁ፡-

- በክልሉ የሚገኙትን የተለያዩ ቅርሶችን ይዘረዝራሉ
- ቅርሶችን የመጠበቅ ፍላጎት ያሳያሉ
- ዋና ዋና የሀገር ጎብኝዎችን ፍላጎት ይለያሉ

2. ዝርዝር ይዘቶች
    - ታሪካዊ ቅርሶች
    - ሃይማኖት
    - የአገር ጎብኝዎች መስሁብ
    - ቅርሳችንን መጠበቅ

## 3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

ቅርሶች የሚለውን ርእስ ሲያስተምሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎች ቅርሶቹን መጎብኘት የሚችሉበት አጋጣሚ ካለ ይጠቀሙበት ። በደ.ብ.ብ.ህ.ክልል በዓይነትም ሆነ በቁጥር ብዙ ቅርሶች ሊኖሩ የቻሉበት ምክንያት የብሄሮችና ብሄረሰቦች በጂኦግራፊ ፣በጎሣና በባህል ቅርርቦሽ መፍጠር ናቸው። ይህንን እውነታ በንባብ እያዳበሩ ትምህርቱን ይስጡ።

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ ቅርሶች ጥቂት ናቸው ። ለምሳሌ ስለ ሀይማኖት ፣ ስለ ሙዚቃና የሙዚቃ መሣሪያዎች ስለጥበባት ሥራ፣ ስለባህላዊ ዕቃዎች አሰራር፣ ስለ ሀውልቶችና ትክል ድንጋዮች ወዘተ በእርስዎ በኩል በተረታ ተረት መልክ (በአፈታሪክ) የሚነገሩ እውነታዎች ከተማሪዎቹ ሊንጸባረቁ ይችላሉ እና ያውጣጧቸው።

ይህንን ታሳቢ በማድረግ በቡድን ለሚያደርጉት ውይይት ሰፊ ጊዜ በመስጠት ወደ ቤተሰቦቻቸው ሲሄዱም ጠይቀው የሚመጡትን ጥያቄዎች በማዘጋጀት ትምህርቱን ማስፋት ይቻላል። ለምሳሌ የኮንሶ ህዝቦች የእርከን ሥራ የጋሞዎች ጥበብ ሥራ ወዘተ በክልሉ ብርቅዬ ቅርሶች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ።

ጠቃሚ ባህል በራሱ አንድ ቅርስ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህም ቅርሶችን በመንከባከብ በኩል ተማሪዎች ተገቢውን ግንዛቤ እንዲይዙ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብዎታል።

ከቅርሶች ውስጥ አንዱ ሙዚቃ መሆኑ በመማሪያ መጽሐፍ ሠንጠረዥ 4.7 ውስጥ ተጠቅሷል። በሁሉም በክልሉ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ዘንድ ሙዚቃ አለ። ባህላዊ ጭፈራውም የሚደነቅ ነው። ይሁንና አዲሱ ትውልድ ባህላዊ ሙዚቃዎችንም ሆነ ባህላዊ አለባበሶችን እየተወ ወደ ባህር ማዶ ሙዚቃና ጭፈራ እዲሁም የልብስ ፋሽን መዞሩ በጣም አሳሳቢና ተገቢም እንዳልሆነ በተማሪዎቹ አእምሮ ውስጥ መቅረፅ ይጠበቅብዎታል!

እንደዚሁም ታላላቅ ሰዎችንና የእድሜ ባለፀጋዎችን የማክበሩ ጉዳይም እየተረሳ መምጣቱን በማንሳት በተማሪዎች ዘንድ ትኩረት እንዲሰጠው ያድርጉ። አዛውንቶች የእውቀት ምንጭ ፣ የባህል መፍለቂያና ማቆያ በመሆናቸው ሊከበሩ እንደሚገባቸው ተማሪዎች እንዲረዱ በማድረግ ድርሻዎን

ይወጡ። ቅርሶችና አገር ጎብኚዎች /ቱሪስቶች/ በእጅጉ የተሳሰሩ ነገሮች መሆናቸውንና በክልሉ የሚገኙትን ቅርሶች ማስጎብኘት እንዲቻል ተማሪዎች ክልላቸውን ለማስተዋወቅ ዝግጁ እንዲሆኑ ማነሳሳት ያስፈልግዎታል። ከዚህም ባሻገር ወደ ክልሉ ለሚመጡ አገር ጎብኚዎች ትህትና ማሳየት ፣ ማስተናገድና መብቶቻቸውን መጠበቅ ተገቢ መሆኑን ተማሪዎች እንዲረዱት ያድርጉ ።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- በአካባቢ የሚገኙ ቅርሶችን (ካሉ) ማስጎብኘት
- በቱሪዝም ቢሮ የሚዘጋጁ ፖስተሮችና
- መማሪያ መጽሀፍ የተጠቀሱ ሥዕሎች ።

## 5. የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎች

ቅርሶች የሚለውን ርእስ እያስተማሩና ከአስተማሩም በኋላ የእያንዳንዱን ተማሪ ሥራ በተከታታይ ይመዝኑ ። መገምገሚያው /መመዘኛው/ ከዚህ በታች ከተቀመጠው ጥሩ ብቃት ጋር በማነፃፀር የተፈለገውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጡ። ጥሩ ብቃት ላይ የደረሱ ተማሪዎች

- የአካባቢያቸውን ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችን ይሰበስባሉ/ ያስሳሉ።
- ቅርሶቻቸውን ለመጠበቅ ዝንባሌ ያሳያሉ።
- የክልላቸውን አበይት የቱሪስት መስህቦች ይለያሉ።
- ለባህላዊ አልባሳትና መዚቃዎች ቅድሚያ ይሰጣሉ፣ይቆረቆሩላቸዋል።
- አገር ጎብኝዎችን የማክበር፣የማስተናገድና የመርዳት ዝንባሌ ይኖራቸዋል።
- ከላይ የተቀመጡትን የመገምገሚያ መስፈርቶችን ተከትለው ሲገመገሙ ተማሪዎችዎ፡-
    1) ተፈላጊውን ደረጃ፣
    2) ከተፈላጊው ደረጃ በላይ የሚያመጡና
    3) ከተፈላጊው ደረጃ በታች የሚያመጡ ይኖራሉ።

ከተፈላጊው ደረጃ በላይ ውጤት ያስመዘገቡትን ማመስገንና መሸለም ይገባዎታል። ከተፈላጊው ደረጃ በታች ያስመዘገቡትን ተማሪዎች የማስተማር ዘዴዎችን በመቀየር ተጨማሪ ጊዜ ወስደው የማብቃት ሥራ ሊሠሩ ይገባዎታል።

### የመልመጃ 4.5 መልሶች

ሀ/ 1. ሃሰት
2.እውነት
3. እውነት
4. ሃሰት
5. እውነት

ለ/ 1. ይህ በጣም አሳሳቢ ችግር ነው ። ይህም ሊሆን የቻለው ወደ አገራችን የሚገቡ የተለያዩ ያላስፈላጊ ፊልሞችና የነጮች ባህል ያመጡት ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ወጣቱ የሀገሩን ባህላዊ ልብሶች እንዲወድ የሚያደርግ ትምህርት በበቂ ሁኔታ ያለማግኘት ችግርም አለ።

2. ይህም ሌላው ችግር ነው በጥያቄ አንድ ላይ የተጠቀሰውና ከውጭ ወደ አገራችን የሚጎርፍ ቪዲዮዎ፣ፊልሞችና ሌላም የማይፈለጉ የባህል ወረራዎች ናቸው ።
3. ታላላቆች ባህልን ያቆዩልን ፣ሀገርን ከጠላት ጠብቀው ያስረከቡን የእውቀት ምንጭ ቢሆኑም የሚሰጣቸው ክብር እየቀነሰ ሄዷል። ይህም በጥያቄ 1 እና 2 ላይ የተመለከቱት ችግሮች ናቸው ።

መፍትሄ - የባህር ማዶ ባህል ወረራን ለመከላከልና የራሳችንን ባህል ለማቆየት

1. ከውጭ በሚገቡት ፊልሞች ፣ ቪዲዮዎችና ሌሎች ባህሎች ላይ የጠበቀ ቁጥጥር ማድረግ
2. ወጣቱን በተለያዩ መንገዶች ስለባህላችን መጠበቅ ሰፊ የሆነ ትምህርት መስጠት

## 4.6 በክልሉ አገር ወዳድነት

የተመደበለት ጊዜ - **10** ክፍለ ጊዜ

**1.** ዝርዝር ዓላማዎች ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ፦

- የክልላቸውን ጀግኖች ስሞች ያውቃሉ
- የጀግኖቹን ማንነት ከሥራቸው ጋር በማገናኘት ይናገራሉ
- የአካባቢያቸውን ጀግኖች አኩሪ ተግባር ያደንቃሉ
- የክልላቸውን ጀግኖች አኩሪ ተግባር በአርአያነት ይከተላሉ

**2.** ዝርዝር ይዘቶች

- አገር ወዳዶች /ጀግኖች/

**3.** የመማር -ማስተማር ክንውኖች

ይህን ይዘት ሲያስተምሩ በፕሮጀክት መልክ ከአገር ወዳዶቹ ጋር ሰፋ ያለ ጊዜ ወስደው በመህል ሌላ ርእስ እያስተማሩ የሚያሳኩት ቢሆን ይመረጣል ።

ዋናው ቁምነገር የአገር ወዳዶችን ስምና ሥራ ማስተዋወቅ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎችን በሚፈልጉት የሥራ መስክ ወደፊት ስኬታማ እንዲሆኑ ማነሳሳት ነው።

ይህ ደግሞ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም ከአካባቢ አርበኞች ጋር ተገናኝተው ከአንደበታቸው እየሰሙ፣ በዓይናቸው እያዩ ሲማሩ ፍሬያማ ይሆናሉ ። በሌላ አባባል አንድ አርበኛ ወይም አገር ወዳድ በሰሩት ሥራ ላይ የሚሰጡት የአንድ ጊዜ ትምህርት ብቻ በቂ አይሆንም። በቂ የማይሆንበት ምክንያት ተማሪዎቹ በተለያዩ ፍላጎቶቻቸውና ተሰጥኦዎቻቸው መታነፅ ስለሚገባቸው ነው። ለምሳሌ

- በስፖርት ውሃ ዋና የእግር ኳስ ወዘተ
- በአትሌቲክስ -አጭር ሩጫ፣ማራቶን ወዘተ
- አካባቢ ጥበቃ -በደን ፣አፈር ፣ አየርና ውሃ ጥበቃ
- በሥዕል የሚሰማሩና ራዕይ ማስቀመጥ የሚፈልጉ ስላሉ ነው።
- ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተጠቀሱት የሙያ መስኮች ታዋቂ የሆኑ አገር ወዳዶችን ለማፍራት በተጨባጭ ስኬታማ የሆኑትን አርበኞች ወደ ክፍል እየጋበዙ ትምህርቱን ማስተላለፍ ይጠበቅብዎታል።

መምህር! አገር ወዳዶችን (አርበኞችን) ለማግኘት ችግር ሊኖር እንደሚችል ይታወቃል።

የቦታ ርቀት፣ የጊዜ ማጣትና የመሳሰሉት ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ሆኖም ያለውን አማራጭ አሟጠው በመጠቀም የነገ አገር ተረካቢ የሆኑትን ህፃናት እድል ለማቃናት መስዋዕት መክፈል የግድ ይሆናል።

ትልቁ ሥራ አገር ወደዶችን የማሳመን ሥራ ነው። አንዳንዴ ተማሪዎቹን ወደ አርበኞቹ መውሰዱ ሊቀል ይችላል። ተማሪዎቹ እያዩ እና እየሰሙ በተጨባጭ መማር መተኪያ የሌለው የማስተማሪያ መንገድ ነውና!

ከትምህርታቸው መልስ ማለትም ከአርበኞቹ በቂ መግለጫና ማብራሪያ ከአገኙ በኋላ ተማሪዎቹ የአርበኞቹን ፈለግ ለመከተል ራዕይ እንዲኖራቸውና በፕሮግራም መመራት እንዲችሉ መርዳት አለብዎት። ተማሪዎች እንደ አቅማቸውና እንደፍላጎታቸው ከቀላል ነገር መጀመር ይገባቸዋል።

ምሳሌ - ከጓሮ አትክልት ልማት

- ከዶሮ እርባታ
- ከአካባቢ ጥበቃ ( ውስን አካባቢ)
- ጠዋት ጠዋት የሩጫ ልምምድ ወዘተ ማካሄድ

ይህ ሲሆን በሰፈርም ሆነ በት/ቤቱ አቅጣጫ የሚያስይዛቸው (አማካሪ) እንዲኖራቸው ማስታወስ አለብዎት። በመጨረሻም የክፍለ ትምህርት አራት ማጠናቀቂያ ላይ ስለ ደረሱ የማጠቃለያ ትምህርት ቢሰጡ ይመረጣል።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የልማት አርበኞች
- የልማት አርበኛ ፎቶ
- የልማት አርበኞች ሜዳልያ

## 5. የመከተታያና መገምገሚያ ዘዴዎች

መምህር! ይህን ይዘት ለማስተማር የተነደፉት ዓላማዎች በትክክል ግባቸውን መተው እንደሆነ ሰማወቅ ትምህርቱን እያስተማሩም ሆነ ከአጠናቀቁ በኋላ የተማሪዎችን ሥራ መገምገም ይጠበቅብዎታል።

ተማሪዎች በጥሩ ብቃት ላይ ናቸው የሚባሉት

- ሰዎች አገር ወዳዶች/አርበኞች/ለመሆን ምን ምን መሥራት ወይም ማሟላት እንደሚገባቸው ለመዘርዘር ሲችሉ ነው።

- እንደክልላቸው የልማት አርበኞች ማለትም አገር ወዳዶች ውጤታማ ለመሆን ራእይ ሲኖራቸው ነው።

  ከጥሩ ብቃት በላይ ላስመዘገቡት ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት እና ምሥጋና ሊሰጧቸው ከቻሉ ተማሪዎቹ ለላቀ ውጤት ይነሳሳሉ።

  ከጥሩ ብቃት በታች ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች የማስተማሪያ ዘዴዎችን ፈትሸውና ተጨማሪ ጊዜ ወስደው የማብቃት ሥራ መሥራት ይጠበቅብዎታል።

## መልመጃ 4.6.

- የመልመጃ **4.6** መልሶች እንደየ ተማሪዎቹ አካባቢ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ።

### የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

ሀ.

| | |
|---|---|
| 1. ሃሰት | 6. ሃሰት |
| 2. እውነት | 7. ሃሰት |
| 3. እውነት | 8. ሃሰት |
| 4. እውነት | 9. እውነት |
| 5. እውነት | 10.ሃሰት |

ለ.

| | |
|---|---|
| 1. መ | 4. ሀ |
| 2. ሐ | 5. ረ |
| 3. ለ | 6. ሠ |

ሐ.

1. ሀ
2. ለ
3. ለ
4. ሀ
5. ለ
6. መ
7. ሐ
8. ሀ
9. መ
10. ለ